እፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 277 ሰኔ 7 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




# ሚኒስቴሩ ለጸረ ተባይ ርጭት የሚውሉ አምስት አውሮፕላኖችን ገዛ

## - አውሮፕላኖቹ ሰደድ እሳትን ለመከላከል እንደሚያግዙም ተጠቁሟል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ግብርና ሚኒስቴር የአንበጣ መንጋና የግሪሳ ወፍ በሰብል ምርት ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ለመከላከል፣ ለአየር ላይ አሰሳ እና ጸረ ተባይ ኬሚካል ርጭት የሚያገለግሉ አምሥት አውሮፕላኖችን መግዛቱን አስታወቀ። አውሮፕላኖቹ የሰደድ እሳትን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር ላይ እንደሚሰማሩም ተነግሯል፡፡

የአንበጣ፣ የግሪሳ ወፍና ተዛማጅ የሰብል ተባዮች የአየር አሰሳና ቁጥጥር ክወና መርሃ ግብርን አስመልክቶ ሚኒስቴሩ በትናትናው ዕለት መግለጫ ሰጥቷል፡፡

በሚኒስቴሩ የእጽዋት ጥበቃ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ በላይነህ ንጉሤ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የገዛቸው ኤርትራክተር 802 በመባል የሚታወቁ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያሟሉ የርጭት አውሮፕላኖች የተገዙት በዋናነት የበረሃ አንበጣና የግሪሳ ወፍን ለመቆጣጠርና ለመከላከል ነው፡፡

ሚኒስቴሩ ለጸረ ተባይ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል



አቶ አስራት ቀጀላ

# ኢትዮጵያ በአቪዬሽን ደህንነት ዘርፍ ምንም አይነት ስጋት እንደሌለባት በኦዲት ተረጋገጠ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በአቪዬሽን ደህንነት ዘርፍ ምንም አይነት ስጋት እንደሌለባት የዓለም አቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በኦዲት ማረጋገጡን የሲቪል አቪዬሽን ደህንነት መምሪያ አስታወቀ፡፡

የተባበሩት መንግሥታት አካል በሆነው የዓለም አቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት

ኢትዮጵያ በአቪዬሽን ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል



አቶ ሚሊዮን ማትዮስ

# በኦጋዴን ከ21 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ በላይ የተፈጥሮ ጋዝ መኖሩ ተረጋገጠ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በሶማሌ ክልል ኦጋዴን በተደረገ ዳሰሳ 21 ቢሊዮን 336 ሚሊዮን ኩቢክ ሜትር የተፈጥሮ ጋዝ እንዳለ መረጋገጡን የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማትዮስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በሶማሌ ክልል ኦጋዴን በተደረገ ዳሰሳ 21 ቢሊዮን 336 ሚሊዮን

በኦጋዴን ከ21... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለመጨመር አዎንታዊ ርምጃ እየተወሰደ ነው

## - ‘የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚነት’ ስምምነት ተፈርሟል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ቀጥተኛ የውጭ የኢንቨስትመንትን ለመጨመርና ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ ለመፍጠር የሚጠቅሙ አዎንታዊ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ መሆኑን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታወቀ። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የገዳ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ኮርፖሬሽን ለኢንቨስተሮች ምቹ መደላድል መፍጠር የሚያስችል “የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚነት” ስምምነት ትናንት ተፈራርመዋል።

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ዘለቀ ተመስገን (ዶ/ር) በወቅቱ ባደረጉት ንግግር፤ ኮሚሽኑ የኢትዮጵያን ብሎም የአፍሪካንና የዓለምን አሁናዊ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ሁኔታን በተገቢው መንገድ በመገንዘብ ለውጭ ቀጥተኛ የኢንቨስትመንት መጨመርና ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ ለመፍጠር ይጠቅማሉ ያላቸውን አዎንታዊ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

የውጭ ቀጥተኛ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል








ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)

## ወጣቶች የለውጥ አራማጅ የሚሆኑበትን የተሳትፎ ባህል ማዳበር ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ወጣቶች ተመልካች ብቻ ሳይሆን የለውጥ አራማጅ የሚሆኑበትን የተሳትፎ ባህል ማዳበር ይገባል ሲሉ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) ገለጹ።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከተባበሩት መንግሥታት የህፃናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) ጋር በመተባበር U-Report Ethiopia የተሰኘ መተግበሪያ ትናንት ይፋ አድርጓል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ 70 በመቶ የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል ወጣት በመሆኑ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ባህል ማሳደግ ይገባል።

ወጣቶች ተመልካች ብቻ ሳይሆን የለውጥ አራማጅ የሚሆኑበትን የተሳትፎ ባህል ለማዳበር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ወጣቶች ቴክኖሎጂን በመጠቀም በነጻ ሃሳባቸውን የሚለዋወጡበትና ወቅታዊ መረጃን እንዲያገኙ የሚረዳ U-Report Ethiopia የተሰኘ መተግበሪያ ከዩኒሴፍ ጋር በመተባበር ይፋ መደረጉን አመላክተዋል።

መተግበሪያው በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ፣ ለዘላቂ ሰላም ግንባታና ለሀገራዊ ጥቅም የሚበጁ ሃሳቦችን ከማንጸባረቅ ባለፈም የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶችን ለማሳለጥ፣ የወጣቱን ስብዕና ለመገንባት እና አምራች ዜጎችን ለመፍጠር ይረዳል ብለዋል።

የወጣቶችን የስራ ፈጠራ ለማስተዋወቅ፣ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ፣ በማህበረሰቡ መካከል ትስስርን ለማጠናከር፣ ለፖሊሲ አውጪዎች ግብዓት ለማቅረብ እና ወጣቶች በሀገራቸው ጉዳይ በነጻነት እንዲሳተፉ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ጨምረው ገልጸዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ወጣቶችን፣ በወጣቶች የሚመሩ ድርጅቶችን፣ ትምህርት ቤቶችን እና ማህበረሰቦችን የሚያገናኝ ሁሉን አቀፍ ስትራቴጂ ለመዘርጋት እና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መሥራቱን ተናግረዋል።

ወጣቶች በሀገሪቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ወጣት የህብረተሰብ ክፍል በቴክኖሎጂ፣ በልማት ሥራዎች፣ በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በኢትዮጵያ የዩኒሴፍ ተወካይ አቡበከር ካምፖ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ዩኒሴፍ ወጣቶችን በቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ U-Report Ethiopia የተሰኘ መተግበሪያ ይፋ አድርጓል።

መተግበሪያው ከዚህ በፊት በ99 የዓለም ሀገራት ተግባራዊ ሲደረግ በርካታ ውጤት እንደተገኘበት ገልጸው፤ የኢትዮጵያ ወጣቶችንም ተጠቃሚ ለማድረግ 100ኛ ሀገር ሆና ተቀላቅላለች ብለዋል።

እንደ አቡበከር (ዶ/ር) ገለጻ፣ መተግበሪያው በኢትዮጵያ በሙከራ ደረጃ ተግባረዊ ሲደረግበት በነበሩት ጊዜያት ከ13 ሺህ በላይ ወጣቶች ተመዝግበዋል። በቀጣይ ሁሉንም ወጣቶች ተደራሽና ተጠቃሚ ለማድረግ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የማስተዋወቅ ሥራው በስፋት እንደሚሠራ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ፕሬዚዳንት ፉአድ ገና በበኩላቸው፤ መተግበሪያው ወጣቶችን በቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ ለሁሉም ወጣቶች ተደራሽ ለማድረግና ተፈጻሚ እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

## የአርሶ አደሮችን ምርታማነት ለማሳደግ ያለመ የፈጠራ ሃሳብ ውድድር ተጀመረ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

<AG/ /YOUTH/ /TECH> AYuTe Africa CHALLENGE | Ethiopia
HEIFER INTERNATIONAL

አዲስ አበባ፡- የአርሶ አደሮችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ያለመ የግብርና፣ ወጣቶችና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሃሳብ ውድድር ትናንት ተጀመረ።

ውድድሩን ያዘጋጀው የሄፈር ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ፕሮግራም ዳይሬክተር አቶ ጢሞቲዎስ ሀዬሶ እንደገለጹት፤ ውድድሩ አዩቴ ኢትዮጵያ የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን፤ የወጣቶችን የግብርና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ሃሳብ በመጠቀም ዘርፉን ለመለወጥ ያለመ ነው።

በውድድሩ አነስተኛ ይዞታ ማሳ ያላቸው ኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮችን ምርትና ምርታማነት እንዲሁም ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ የሚረዱ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ሃሳቦች እንደሚቀርቡ አመላክተዋል። አሸናፊ የፈጠራ ሃሳቦችን በመሸለምና ዕውቅና በመስጠት ለማበረታታት፣ የገንዘብ ድጋፍና ሙያዊ እገዛ በመስጠት ሥራዎቻቸውን ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

በአዩቴ ኢትዮጵያ ውድድር ላይ ለመሳተፍ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 30 የሆኑና ግብርናን ለማሻሻል የሚረዳ የፈጠራና ቴክኖሎጂ ሃሳብ ያላቸው ኢትዮጵውያን ወጣቶች መወዳደር እንደሚችሉ ገልጸዋል። አቶ ጢሞቲዎስ እንዳስታወቁት፤ ለውድድሩ ከሚቀርቡ ፈጠራዎች መካከል በመስኩ የላቀ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎችና ዳኞች ተመዝነው የሚያልፉ 30 ሃሳቦች ለመጀመሪያው ዙር ውድድር ያልፋሉ።

በመቀጠል ከመጀመሪያው ዙር 30 ተወዳዳሪዎች ውስጥ 10 የተሻለ ሃሳብ ያቀረቡ ተወዳዳሪዎች ተለይተው ወደ ሥልጠና ፕሮግራም እንዲገቡ ይደረጋል ያሉት ፕሮግራም ዳይሬክተሩ፤ የፈጠራ ሃሳባቸውን ለማሳደግ የተሻለ የሚያስችል በቂ ሥልጠናና ድጋፍ ካገኙ በኋላ የተሻለ ውጤት ያመጡ ሦስት አሸናፊዎች በየደረጃው ይሸለማሉ ብለዋል።

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የኢኖቬሽን ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሰላምይሁን አደፍርስ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ አዩቴ ኢትዮጵያ የፈጠራ ሃሳብ ውድድር የማህበረሰቡን ኑሮ ሊያሻሽሉ የሚችሉ ቴክኖሎጂ ውጤቶች የሚገኙበት መድረክ ነው።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሀገሪቱ የፈጠራ ባህል እንዲዳብር ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው ያሉት አቶ ሰላም ይሁን፤ ጀማሪ የቢዝነስ ሃሳቦች ፈጠራ መር እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር ሥራ እያከናወነ ይገኛል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

በተበታተነ መልኩ የሚካሄዱ የፈጠራ ውድድሮችን በተደራጀ መልኩ እንዲሄዱ የሚያደርግ የግንኙነት ሥራዎችንም እየሠሩ መሆኑን አመላክተው፤ የሳይንስና ፈጠራ ውድድሮች በልማት አጋሮች መልካም ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረቱ እንዳይሆኑ የሚያግዝ የስትራቴጂክ ማዕቀፍ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

በውድድሮቹ ውጤታማነት ላይ የልማት አጋሮች ያላቸው ድጋፍ ከፍተኛ መሆኑን አንስተው፤ ሥራው በቀጣይነት እንዲከናወኑ መንግሥትን ጨምሮ የሌሎችም ባለድርሻዎች ባለቤትነት ወሳኝ መሆኑን አስረድተዋል።

አዩቴ ኢትዮጵያ የፈጠራ ሃሳብ ውድድር በአጠቃላይ የ20 ሺህ ዶላር የገንዘብ ሽልማት የተዘጋጀ ሲሆን፤ አንደኛ ለሚወጣ 10 ሺህ ዶላር፣ ሁለተኛ ደረጃ ለሚይዝ 6 ሺህ 500 ዶላር እንዲሁም ሦስተኛ ደረጃ ለሚወጣ ደግሞ 3 ሺህ 500 ዶላር እንደሚበረከት ታውቋል።

የፈጠራ ሃሳብ ያላቸው ወጣቶች እስከ ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በመወዳደሪያው ድረገፅ (https://ayute- Ethiopia.et/apply-here/) ሃሳቦቻቸውን አቅርበው መሳተፍ እንደሚችሉ ተገልጿል።



## ክልሉ 46 ሺህ ቶን ቡና ለማዕከላዊ ገበያ አቅርቧል

### - 71 ሚሊዮን የቡና ችግኝ ለመትከል ዝግጅት ተደርጓል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ ባለፉት 11 ወራት 46 ሺህ ቶን የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ መቻሉን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል አስታወቀ፡፡ በመጪው ክረምት 71 ሚሊዮን የተለያየ ዝርያ ያላቸው የቡና ችግኞች ለመትከል ቅድመ ዝግጅት መደረጉን ክልሉ ጨምሮ ገልጿል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አስራት መኩሪያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በክልሉ 46 ሺህ ቶን የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ ተችሏል፡፡

እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ 67 ሺህ 348 ቶን የቡና ምርት ወደ ማዕከላዊ ገበያ ለመላክ ታቅዶ ባለፉት 11 ወራት 46 ሺህ ቶን ቡና ወደ ማዕከላዊ ገበያ ተልኳል ያሉት አቶ አስራት፤ የተመረተው የቡና ምርትም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲሁም ለውጭ ገበያ የሚላክ ነው ብለዋል፡፡

አቶ አስራት አክለውም፤ ከሥራ እድል ፈጠራ አንጻር አጠቃላይ ከቡና ሻይና ቅመማ ቅመም በተለይ ለሴቶችና ወጣቶች በቋሚነትና በጊዜአዊነት 49 ሺህ 644 የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን ጠቁመዋል፡፡

በክልሉ በዘርፉ ያለውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለማሳደግና አርሶ አደሩ ባመረተው ልክ ተጠቃሚ እንዲሆን የገበያ ትስስሩ ላይ ይበልጥ ትኩረት መደረጉን አቶ አስራት አስረድተዋል፡፡

በዚህ በጀት ዓመት በመኸር ወቅት የሚተከል 71 ሚሊዮን የቡና ችግኝ ከሚያዚያ ወር ጀምሮ ዝግጅት ሲደረግ መቆየቱን ጠቅሰው፤ እስካሁን የጉድጓድ ዝግጅት እንዲሁም በክልሉ ያለው የዝናብ ስርጭትን ተከትሎ ተከላ መጀመሩን አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ አስራት ገለጻ፤ በክልሉ አሁን ላይ ያለው የአየር ሁኔታ ሻይ፣ ቡናና የተለያዩ ቅመማ ቅመሞች በሰፊው ለማምረት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡ ተከላው እስከ መጪው ነሃሴ ወር ድረስ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በመኸር የሚተከለው የቡና ችግኝ በንቅናቄ በአርሶ አደሩ እንዲተከሉ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑንም ነው አቶ አስራት ያስታወቁት፡፡

በተለይ የተከላ ሥራው ከአረንጓዴ ዐሻራ ጋር ተቀናጅቶ እንዲሠራ እየተደረገ ነው ያሉት አቶ አስራት፤ በክልሉ የአረንጓዴ ዐሻራ ይበልጥ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲያስገኝ የተለያዩ የፍራፍሬ ችግኞች እየተዘጋጁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ክልሉ ከፍተኛ የቡና ምርት የመስጠት አቅም ያለው በመሆኑ ለቡና ጥላ የሚሆኑ ዛፎች በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ-ግብር አብረው እንዲተከሉ እቅድ ተይዟል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

# በክልሉ ከ612 ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**



ጋምቤላ፡- በጋምቤላ ክልል በፌዴራል መንግሥት የተጀመሩ ከ612 ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመት ያላቸው ዘጠኝ የመንገድ ፕሮጀክቶች በሥራ ላይ መሆናቸውን የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡመድ ኡጁሉ ገለጹ፡፡

የጋምቤላ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡመድ ኡጁሉ እንደገለፁት፤ የመሠረተ- ልማት ዘርፍ ጥራቱን የጠበቀ ፍትሃዊ የመሠረተ ልማት ሥርጭት ለማረጋገጥ በለውጡ ዓመታት የክልሉ መንግሥት ከፌዴራል መንግሥት ጋር በቅንጅት እየሠራ ይገኛል፡፡ በርካታ የመንገድ፣ የመብራትና የቴሌኮም ማስፋፊያ ተግባራትም ተከናውነዋል፡፡

በመንገድ መሠረተ ልማት፣ ጤና ተቋማት፣ የትምህርት ተቋማትና ሌሎች የኤሰቲ መሠረተ ልማቶችም በሰፊው እንደተሠሩ የተናገሩት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በመንገድ ልማት ዘርፍ አያሌ ተግባራት በመከናወን ላይ መሆናቸውን አስገንዝበዋል፡፡

ከለውጡ በፊት የጎሬ-ጋምቤላ የአስፋልት መንገድ ብቻ የነበረ መሆኑን አንስተው፤ በአሁኑ ሰዓት በፌዴራል መንግሥት የተጀመሩ 612 ነጥብ 24 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያላቸው ዘጠኝ የመንገድ ፕሮጀክቶች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡

ከፕሮጀክቶቹ ውስጥ አቦቦ-ሜጢ፣ ጎግ-ጆር-አኮቦ፣ ጋምቤላ-አቦቦ-ዲማራድ፣ ላሬ-ጂካዎ-ኘንኖንግ እና ፒኘውዶ-ጊሎ ወንዝ እንዲሁም አኩላ-አቻኛ በተሻለ የግንባታ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል፡፡ ፕሮጀክቶቹን በፍጥነት በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ለማብቃት ርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝም አስረድተዋል፡፡


እንደ ርዕሰ መስተዳድሩ ገለፃ፤ በራስ አቅምና በአጋር አካላት ትብብር የሚገነቡትን በሚመለከትም በወረዳዎች ያለውን የመንገድ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በስምንት ወረዳዎች ከ80 ኪ.ሜ በላይ የሆኑ የገጠር መንገዶች ተጠናቅቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆነዋል፡፡ በአጠቃላይ ቀበሌ ከቀበሌ የሚያገናኝ የጠጠር መንገድ አጠቃላይ የመንገድ ኔትወርክ ርዝመት በ2010 በጀት ዓመት ከነበረው አንድ ሺህ 530 ኪሎ ሜትር ርዝመት በ2016 በጀት ዓመት ወደ ሁለት ሺህ 153 ኪ.ሜ ለማድረስ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ በቴሌኮም ዘርፍ በርካታ ሥራዎች እየጠሡሩ እንደሚገኙም አቶ ኡመድ ተናግረዋል፡፡

ከለውጡ በፊት በከተማ ብቻ የተወሰነው የስልክ ተደራሽነት በአሁኑ ሰዓት አገልግሎት ከአኮቦ ወረዳ በስተቀር በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ከተሞችና ወረዳዎች በከተማው ውስጥ ቋሚ የስልክ መስመር ወይም የቤት ስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋልም ብለዋል፡፡

የሞባይል እና የኢንተርኔት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በብሮድባንድ፣ 2ጂ እና 3ጂ የኔትወርክ አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሆኑም አብራርተዋል፡፡

ጋምቤላ፣ ፒኘውዶ፣ አቦቦ፣ ኢታንግ፣ ሜጢ እና ዲማ ከ2014 ጀምሮ የ4ጂ LTE አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል፡፡



# ከ3 ሺህ 500 በላይ ተማሪዎች የሚሳተፉበት የሒሳብ ውድድር ሊካሄድ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ከሦስት ሺህ 500 በላይ ተማሪዎች የሚሳተፉበት ስድስተኛው ዙር ሀገር አቀፍ የሒሳብ ትምህርት ውድድር ሊካሄድ መሆኑ ተገልጿል።

ከሐምሌ 28 እስከ ነሀሴ አንድ ቀን 2016 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ የሚካሄደውን ሀገር አቀፍ የሒሳብ ትምህርት ወድድር አስመልክቶ አዘጋጁ ማይ ሶሮባን ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ትናንት መግለጫ ሰጥቷል፡፡

የማህበሩ መስራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ከበደ አጥናፍ በወቅቱ እንደተናገሩት፤ በሒሳብ ትምህርት ወድድሩ አጠቃላይ ከ50 ከተሞች የሚመጡ ተማሪዎች ይሳተፋሉ፡፡ ከአንድ ከተማ 70 ተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ ሲሆን፤ በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሦስት ሺህ 500 በላይ ተወዳዳሪዎች ይሳተፋሉ ብለዋል።

የውድድሩ ጥያቄዎች በአማርኛና በእንግሊዝኛ እንዲሁም ተማሪዎች ከሚመጡባቸው አካባቢዎች ከሚወሩ ቋንቋዎች እንደሚዘጋጁ አመላክተዋል። አንድ ተማሪ በሚችለው ቋንቋ እንዲወዳደር ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አቶ ከበደ እንደገለጹት፤ የፈተና ወድድሩ የተዘጋጀው ከሶስተኛ እስከ 12 ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ነው፡፡ በሀገር አቀፍ ውድድሩ አሸናፊ ለሚሆነው ተማሪ የ50 ሺህ ብር፣ የሜዳሊያና የዋንጫ ሽልማት እንደሚሰጥ አመላክተዋል፡፡

አቶ ከበደ እንደተናገሩት፤ የወድድሩ ዓላማ የሒሳብ ትምህርት ይከብዳል የሚለውን አስተሳሰብ ለመቀየር ፤ በሒሳብ ጥሩ እውቀት ላላቸው ተማሪዎች እውቅና ለመስጠትና ኢትዮጵያን ወክለው በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ የትምህርት ወድድሮች ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎችን ለማበረታት ነው።

በውድድሩ ሂደት በየከተማው ከሚገኙ የትምህርት ጽህፈት ቤቶች ጋር በጋራ እንደሚሠሩ ጠቁመው፤ ጽህፈት ቤቶቹ በከተማው የሚገኙ ተማሪዎች መጀመሪያ በትምህርት ቤት ደረጃ በማወዳደር እንደሚለዩ አስረድተዋል።

በሌሎች ሀገራት ለተመሳሳይ ውድደሮች መንግሥት እስከ 30 በመቶ ያለውን ድርሻ በመያዝ ድጋፍ እያደረገ ቀሪውን ለግለሰቦች ይለቃል ያሉት አቶ ከበደ፤ በኢትዮጵያም ይህ ልምድ ኖሮ መንግሥት የሒሳብ ትምህርት ውድድር ላይ በመሳተፍ ድጋፍ ቢያደርግ መልካም ነው ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በአጠቃላይ ለውድድሩ አራት ሚሊዮን ብር ሽልማት ተዘጋጅቷል። በተጨማሪ ማይ ሶሮባን ኢትዮጵያ ኮሜዲያን ቤቴልሄም ጌታቸው (ቤቲ ዋኖስ) የውድድሩ የበጎ ፋቃድ አምባሳደር በመሆን ስምምነት አድርጋለች።

# ከግብር ጋር የተያያዙ የሥነ ምግባር ችግሮችን ለመቅረፍ የከፋዩ ተሳትፎ ይጠበቃል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**



**ኮማንደር አሕመድ መሀመድ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ከግብር ጋር የታያያዙ የሥነ ምግባር ችግሮችን ለመቅረፍ የግብር ከፋዩ ተሳትፎ እንደሚጠበቅ ተገለጸ።

በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ የሕግ ማስከበር ዘርፍ ኃላፊ ኮማንደር አሕመድ መሀመድ በመርሃግብሩ ላይ እንደተናገሩት፤ የሥነ ምግባር ጥሰት የሚታየው በግብር ሰብሳቢውም በግብር ከፋዩም በኩል ነው። በመሆኑም ማስተካከያውም ሊደረግ የሚገባው በሁለቱም ወገን ነው።

ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ በአንድ ወገን ራሱን ከሕግ አግባብ ውጪ ከመንቀሳቀስ በመታቀብ በሌላ በኩል ተገቢ ያልሆኑ አካሄዶችን ሲመለከት ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ይኖርበታል ሲሉ አሳስበዋል።

ይህም ሆኖ ቢሮው የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት በዘላቂነት መፍትሄ ለመስጠት ከአደረጃጀት ማስተካከያ ጀምሮ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል ያሉት ኮማንደር አሕመድ፤ የአደረጃጀት ማስተካከያ ሲባል በውስጡ ከሚይዘው መካከል አንዱ የሥነ ምግባር ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለዚህም የገቢዎች ቢሮ የሰው ሃይል የማደራጀት ሥራ ሲያከናውን በየደረጃው የሥነምግባር መኮንን እንዲካተት መደረጉን አንስተው፤ በእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤትም በዳይሬክቶሬት ደረጃ ተቋቁሞ እየሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

ነገር ግን ችግሩን በዘላቂነትና አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለመቅረፍ የተጀመሩ ሥራዎችን በቴክኖሎጂ የማከናወን ተግባራት ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል ብለዋል።

እያንዳንዱ ሥራ ከሰው ንክኪ ነጻ በሆነ ቁጥር የሥነ ምግባር ችግሩም በዛው ልክ እየቀነሰ ይመጣል ያሉት ኮማንደር አሕመድ፤ እስካሁንም የኢ - ፔይመንት እና የኢ -ፋይሊንግ አሠራሮችን በመተግበር ብዙ ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል። አሁንም ግን የደረሰኝ ቁጥጥርን ጨምሮ ሌሎቹንም በቴክኖሎጂ የማከናወን ሥራ ይጠበቃል ነው ያሉት።

አጠቃላይ ካሉት 482 ሺህ ነጋዴዎች ውስጥ የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋይ ከሶስት መቶ በላይ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ እነዚህ ግብራቸውን በቁርጥ በዓመት አንድ ጊዜ የሚከፍሉ በመሆኑ ከሰው ንክኪ እንዲላቀቁ ማድረግ መቻሉን አስገንዝበዋል።

በተጨማሪ ስምንት መቶ የሚደርሱ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ሙሉ ለሙሉ የኢ ፋይሊንግና ኢ ፔይመንት አገልግሎት እየተጠቀሙ ይገኛሉ ብለዋል።

እንደ ኮማንደር አሕመድ ገለፃ፤ በአሁኑ ወቅት በሁሉም ቅርንጫፎች የመረጃ ማጣራት ሥራ እየተከናወነ ሲሆን ሲጠናቀቅ አብዛኛው ሥራ በቴክኖሎጂ የሚሠራ በመሆኑ ለሥነ ምግባር ችግሮችም ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል። ይህም ሆኖ በእያንዳንዱ እንቅስቀሴ የግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ተሳትፎ ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

በመሆኑም ግብር ከፋዩ ማህበረሰብ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ረገድ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል። የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው፤ ግብር መሰብሰብ የመንግሥት ግዴታ እንደሆነ ሁሉ ግብር መክፈልም የንግዱ ማህበረሰብ መብትም ግዴታም መሆኑ መታወቅ አለበት ብለዋል።

የንግዱ ማህበረሰብ ግብሩን መክፈል ያለበት ደግሞ የሕግ አግባብን ተከትሎ ብቻ መሆን ይኖርበታል ነው ያሉት። ግብር ለሀገር ልማትና ብልጽግና ብሎም የኢኮኖሚ እድገት ዘላቂ እንዲሆን ወሳኝ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ለዚህ ደግሞ ጠንካራ የግብር አሰባሰብ ሥርዓት ሊኖር ይገባል ሲሉ ገልጸዋል። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ታክስ የግሉ ዘርፍ ካሉበት ቀዳሚ ችግሮች መካከል አንዱ መሆኑን ተናግረዋል።

የንግዱ ማህበረሰብ ከፖሊሲ ጀምሮ በሕጎች መመሪያዎችና ደንቦች ላይ እንዲሁም በአገልግሎት ወቅት ብዙ ችግሮ እየገጠሙት መሆኑ ይታወቃል። ይህንን ለመፍታት ተቀራርቦ መሥራት የሚጠበቅ ቢሆንም የግብር ሰብሳቢው አካል ዋናውን ድርሻ መውሰድ አለበት ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰቱን የማሳደጉ ሥራ የመላው ሕዝባችንን የተቀናጀ ጥረት ይፈልጋል!

ለአንድ ሀገር የእድገት ጉዞ ስኬት ከሆኑት መካከል የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ትልቅ አቅም እንደሆነ ይታመናል። የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የማይፈልግ ሀገር የለም፡፡ አድገዋል የሚባሉት እንደ ቻይና ያሉት ሀገሮችም ጭምር ይህን የልማት አቅም በእጅጉ ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ኢንቨስትመንት በተለይ ለድሃ እና በማደግ ላይ ላሉ ሀገሮች ደግሞ ትልቅ አቅም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የእነዚህ ሀገሮች የልማት እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን ይህ ኢንቨስትመንት ወሳኝ መሆኑም ይታመንበታል፡፡

እነዚህ ሀገሮች ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት እና አምራች ዜጋ እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ ሀገሮቹ የሚያንሳቸው ወይም የሌላቸው ካፒታል፣ እውቀትና ቴክኖሎጂ ነው፡፡ ደሃ ወይም በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገሮች ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብትና አምራች ዜጋ ለመጠቀም በሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ የሆነ የካፓታል እጥረት ይገጥማቸዋል፡፡ በዚህ ላይ እውቀትና ቴክኖሎጂ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ይህን ሁሉ ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ይታመናል፡፡

ከዚህ በመነጨም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ማፈላለግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ የመወዳዳሪያ መድረክ እየሆነ መጥቷል። ሀገራት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው እየተንቀሳቀሱ ያለበት ሁኔታም በስፋት ይስተዋላል። ውድድሩም በብዙ መልኩ ጠንካራ ሆኖ መገኘትን እየጠየቀ ይገኛል።

ሀገራችን ያላትን ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት እና የሰው ሃይል በስፋት ወደ ልማት ለማስገባት ይህንኑ ዓለምአቀፋዊ እድል አሟጣ ለመጠቀም የሚያስችሉ ጥረቶችን ስታካሂድ ቆይታለች። ይህን ተከትሎ እየተገኘ ያለው ውጤትም ተስፋ ሰጪ ቢሆንም ፤እንደ ሀገር ከዘርፉ ከሚጠብቀው፣ እንዲሁም ለመልማት ካላው ጽኑ ፍላጎጽ አኳያ ሲታይም ገና ብዙ መሰራት እንደሚኖርበት ይታወቃል።

በተለይም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ እንደ ሀገር በልማት ድህነትን ለመሻገር የተጀመረው ሀገራዊ የልማት ንቅናቄ ስኬታማ እንዲሆን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ትልቅ አቅም እንደሆነም ይታመናል ። ይህንን አቅም አሟጦ ለመጠቀም የሚደረገውም ጥረት የሁሉንም አካል ጥረት ይጠይቃል።

የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በዚህ ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም ከፍተኛ ተወዳዳሪነት እየጠየቀ ባለበት አሁናዊ ሁኔታ ፣ የዕድሉ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን በቂ ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠርም ወሳኝ ይሆናል። ከዚህ አንጻር በመንግሥት በኩል እየተደረገ ያለው ጥረት እና እየተመዘገበ ያለው ውጤትም ተስፋ ሰጪ ነው።

ሀገሪቱ ከሀገራት ጋር የምታደርገውን ግንኙነት ስትራቴጂክ ወደሆነ የልማት አጋርነት ከመለወጥ የሚጀምረው የመንግሥት ጥረት፤ ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ ለመፍጠር የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና የሪፎርም ሥራዎችን ተግባራዊ በማድረግ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ከዚህ ቀደም ለውጭ ዜጎች ዝግ የነበሩ እንደ ወጪና ገቢ ንግድ ያሉ ዘርፎች ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ማድረግ ፣ የሀገሪቱን የኢንቨስትመንት አማራጮች ለውጭ ባለሀብቶች ማስተዋወቅ ፣ ሀገር ውስጥ ገብተው መዋዕለ ነዋያቸውን ለሚያፈሱ ባለሀብቶች የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋትም የዚሁ ጥረቱ አካል ናቸው።

በዓመቱ ሦስት የቻይና ኢንዱስትሪዎችና ሁለት የህንድ ኩባንያዎች በሃዋሳ የኢንዱስትሪ ፓርክ ሼዶችን በመውሰድ ሥራ የጀመሩበት ሁኔታም የዚህ ጥረት ማሳያዎች ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ኩባንያዎቹ የሀገሪቱን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በማሳደግ በኩል የጎላ ሚና ነበራቸው።

ከነዚህ ውጭም ሌሎች የቻይና ፣ የኔዘርላንድና የቱርክ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እየተሳተፉ ይገኛሉ ። ከአውሮፓ፣ አሜሪካና ኢሲያ የመጡት ትልልቅ ኩባንያዎችም እንዲሁ በኢትዮጵያ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሥራት ወስነው እየተንቀሳቀሱ ነው።

በቅርቡ ከሳዑዲ አረቢያ ባለሀብቶች ጋር የተደረገው ውይይት እና በውይይቱ ማጠናቀቂያ የታየው ተስፋም ሆነ ፣ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር በሲንጋፖር እና በደቡብ ኮሪያ ጉብኝታቸው ማጠቃለያ ከሀገራቱ ጋር በኢንቨስትመንት ዙሪያ የደረሱባቸው መግባባቶችም እንዲሁ የዚሁ የመንግሥት ጥረት ማሳያዎች ናቸው።

ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ዕድገቱ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተቋቋሙ የሚገኙትና ብዙ ሚሊዮን ዶላር ወጪ የተደረገባቸው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ትልቅ የሚባል አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በሀገሪቱ እየተካሄደ ያለው የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እየጨመረ መሄድ እና መሰል አሁናዊ ልማቱ የፈጠራቸው ዕድሎች ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንቱ ፍሰት አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ።

ይህም ሆኖ ግን ይህንን እድል በአግባቡ እንዳንጠቀምበት ተግዳሮት ሆነው የቆዩት በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚታዩትን የጸጥታ ችግር ፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ፣ የቢሮክራሲ ማነቆዎች ... ወዘተ. ለመሻገር አሁንም የመንግሥትን ብቻ ሳይሆን የመላውን ሕዝብ የተቀናጀ ጥረት ይፈልጋል። ስለ ሰላም ዘብ መቆምን ፤ ጥቁር ገበያን አምርሮ መታገልን ፤የውጭ ባለሀብቶችን የልማታችን አጋር አድርጎ ተቀብሎ አብሮ መሥራትና መንከባከብን ይጠይቃል!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የማንበብ ባህል እንዲዳብር ...

አስማየሁ ግዛው

ሥነ ጽሑፍና ንባብ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ብቻም ሳይሆኑ አብሮ የሚያድድጉና የሚሞቱ የሰው ልጅ የፈጠራ ተግባራት እንደሆኑ ይታመናል:: የንባብ ባህል ሲዳብር የሀገራት ሥነ-ጽሑፍም አብሮ እና ተደጋግፎ ያድጋል:: የንባብ ባህልና ሥነ-ጽሑፉ የሚያድግ ከሆነ ደግሞ የሀገራት የሥልጣኔ ደረጃ እና የትውልድ ግንባታም በዛው ልክ ተያይዞ እንዲያድግ ይረዳል:: ወቅቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንደመሆኑ መጠን የሀገራት የንባብና የሥነ-ጽሑፍ እድገት ፈታኝ ወቅትን እያሳለፈ ይገኛል::

በዳበረ የንባብ ባህል እና የሥነ-ጽሑፍ እድገት በቀዳሚነት የሚጠቀሱት የበለጸጉ ሀገራት መሆኑ ደግሞ የሚያስገርም ነገር ነው:: ሀገራቱ ምንም በሳይንስና በቴክኖሎጂ የረቁቁ ቢሆንም የንባብ ባህላቸውን እና የሥነ-ጽሑፍ እድገታቸውን ሊገታው አልቻለም:: በደህነት እና በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገራት ግን የሚታየው ከዚህ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን::

ቴክኖሎጂው በሀገራቱ የንባብ ባህልና ሥነ-ጽሑፍ እድገት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖን በመፍጠር ላይ ይገኛል:: ይህ እንደ ኢትዮጵያ በሥነ-ጽሑፍ ታሪካቸው በቀዳሚነት ለሚጠቀሱ ሀገራት ጉዳቱ ከፍተኛ ይሆናል:: ብዙ ሊነበቡ የሚችሉና ሀገርን አንድ ርምጃ ማስኬድ የሚችሉ የሃይማኖታዊ፣ የሳይንስ፣ የሥነ-ፈለግ፣ ኢንጂነሪንግ እና ሌሎች የጥንት እውቀቶችን የያዙ ለቁጥር የሚታክቱ መጽሐፍትን የያዘች ሀገር አንባቢ ትውልድን መፍጠር አለመቻሏ ትልቅ ጥያቄን ሊያስነሳ ይችላል::

የኅብረተሰቡ የማንበብ ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ በመምጣቱ የሚመራመር፣ የሚጽፍ፣ እና ለነገሮች ምክንያታዊና ሙያዊ ትንታኔን መስጠት የሚችሉ ሰዎችን ማፍራት ላይ ክፍተቶች እየተፈጠረ ይገኛል:: አሁንም በየቤተ-መጽሐፍቱ እና የሃይማኖት ተቋማቱ ትውድን መቀየርና ሀገርን ማሳደግ የሚችሉ ብዙ እውቀቶችን የያዙ መጽሐፍትን ጥቅም ላይ ለማዋል የኅብረተሰቡን የንባብ ባህል በትልቁ መገንባት ወሳኝ ጉዳይ ነው:: ይህም ሲባል፣ የማንበብ ባህል የሚያሸንፍበት፣ ለንባብ ዋጋ የሚሰጥበት፣ የሚከበርበትን እና የሚበረታታበትን አካባቢ መፍጠር ላይ መሥራት ያስፈልጋል::

ይህ አይነቱ አካባቢም እንዲፈጠር የሚመለከታቸው አካላት ምቹ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ለዚህም ከቤተሰብ በመጀመር፣ በትምህርት ቤት በማስፋት መሠረት ጥሎ የንባቡን ባህል ለማሳደግ ህጻናት ላይ መሥራት ነገሩን በፍጥነት ውጤታማ ማድረግ ይችላል:: ትምህርት ቤት ላይ እና ቤተሰብ ላይ የሚሠራው ሥራ ቤት ሲሠራ ጠንካራ መሠረት እንደመጣል ይቆጠራል:: የሚወጣው የቤቱ መሠረት ጠንካራ ከሆነ ጥሩ አገልግሎት መስጠት የሚችል ቤት እንደሚያደርገው ሁሉ ህጻናት አእምሮ ላይ የሚሠራው ነገር ጥሩ የሆነን አንባቢ ትውልድ መፍጠር ይችላል::

እዚህ ላይ ከትምህርት ቤትና ከወላጆች የሚጠበቀው ሥራና ኃላፊነት ትልቅ ሥፍራን የሚይዝ ይሆናል:: ወላጆች ልጆቻቸው ማንበብን እንዲለማመዱ በእውቀታቸው ልክ መጽሐፍትን ገዝቶ በማቅረብ የወላጅነት ሚናቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል:: ንባብ ላይ የሚሠራው ሥራ ትውልድን የሚያንጽ ከመሆኑም በተጨማሪ የሀገር ግንባታን የሚያቃልል ይሆናል::

ንባብን የሚያነቃቁ፣ የሚያበረታቱ እና የሚጋብዙ ሁኔታዎችን በተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት መፍጠር ሌላው ማሳደጊያና ማዳበርያ መንገድ ነው:: ይህ ጉዳይ በተለይ ለመገናኛ ብዙኃን አበክረውና ጠንክሮ ሊሠሩበት የሚገባው ቀዳሚው አጀንዳቸው መሆን ይገባዋል:: ለዚህ ባህል መዳበር ሌሎችም የሚዲያ ተቋማት ትምህርት ወስደው ሊሠሩ የሚገባው የኤፌም አዲስ 97 ነጥብ 1 “ለተሻለ ነገ እናንብብ” በሚል ሃሳብ የተካሄደው የአንድ መቶ ቀናት የንባብ ዘመቻ ይጠቀሳል:: በዚህ የንባብ ዘመቻ ብዙ ሙሁራን፣ ታዋቂ ሰዎች፣ የሚዳያ ባለሙያዎች እና የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች ተጋብዘው ያነበቧቸውን የምንጊዜም ምርጥ መጽሐፍትን ለአድማጭ ተመልካቾች ማድረስና የንባብ ልምድና ተሞክሮአቸውን አካፍለውበታል::

በዚህም የተነሳ የማህበረሰቡ የማንበብ ፍላጎት መነቃቃትን በማሳየት እና ለማንበብ ፍላጎትን የሚያሳይ ማህበረሰብን ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል:: የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሬዲዮ ጣቢያውን 24 ዓመት የምስረታ ክብረ በዓልንም ሲያከብር፤ ይሄንኑ ከግምት ውስጥ አስገብቶ የመጽሐፍ አውደ ሪዕይን አዘጋጅቶ ተማሪዎች፣ መምህራን እና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች መጽሐፍት ገዝተው እንዲያነቡና የንባብ ባህልን እንዲያሳድጉ ማበረታታት ችሏል::

ተቋሙ የሚዲያ ተቋም እንደመሆኑና ተጽእኖ ፈጣሪነቱም እንዳለ ሆኖ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት እና ኅብረተሰቡ ለንባብ እንዲነቃቃና ባህሉ እንዲያደርግ በአርአያነቱ ይጠቀሳል:: በሀገሪቱ የሚገኙ በርካታ የህትመት፣ የብሮድካስትና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ንባብን ባህሉ ያደረገ ትውልድ ለመፍጠር ሚደረገውን ጥረት በቋሚነት መደገፍና ሰፊ ሽፋን በመስጠት መሥራት ይጠበቅባቸዋል::

> **ኢቢሲ በቀጣይ ዓመትም የቴሌቪዥን ጣቢያውን 60ኛ ዓመት የምስረታ ክብረ በዓል ሲያከብር 6 ሺ መጽሐፍትን አሰባስቦ ለሕዝብ ቤተ መጽሐፍት በስጦታ መልክ ለማበርከት አስቧል**

ኢቢሲ በቀጣይ ዓመትም የቴሌቪዥን ጣቢያውን 60ኛ ዓመት የምስረታ ክብረ በዓል ሲያከብር 6 ሺ መጽሐፍትን አሰባስቦ ለሕዝብ ቤተ መጽሐፍት በስጦታ መልክ ለማበርከት አስቧል:: ይህም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር የንባብ ባህል እንዲዳብር “መጽሐፍትን ቤተኛ” እናድርግ የሚለውን መልዕክትን ለመደገፍና መጽሐፍትን አሰባስቦ በመስጠት ኅብረተሰቡ ለንባብ የሚሰጠውን ትኩረት ለማሳደግም ታስቦ ነው::

የንባብ ባህልን ለማዳበርና ለማሳደግ ተቋማት ከኢቢሲ ተሞክሮ በመውሰድ የተለያዩ አውደ ርዕይዎችን በማዘጋጀት እና ሌሎች ማነቃቅያ መንገዶችን በመጠቀም ሠራተኞቻቸው ብሎም ህብረተሰቡ ንባብን ባህሉ እንዲያደርግ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል:: ማንባብ ለሀገር እና ለትውልድ የሚኖረውን ሚና በሚገባ የማስገንዘብ ሥራን ማስፋትና ባህሉን መገንባት ትልቁ ቦታ ሊሰጠው ይገባል:: ቤተ መጽሐፍትን በሁሉም ቦታ ማስፋት እና በቀላሉ የሚነበብበትን ሁኔታ መፍጠር ሰው ለመጽሐፍት ቅርብ እንዲሆንና ንባብን እንዲለማመድ የሚያግዝ ነጥብ ነው::

ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሰዎች የሚፈልጉትን መጽሐፍት በያሉበት በቀላል ሁኔታ ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር:: ወጣቶችን በንባብ በማሳተፍ እና እንደየፍላጎታቸውና እውቀታቸው እንዲያነቡ መንገዱን ምቹ ማድረግ ጠንካራ የንባብ ባህልን መገንባት ይችላል::

ኅብረተሰብን የሚያሳትፉ ትምህርታዊ ሁነቶችን በማዘጋጀት ታዋቂ ደራሲዎች እና የተለያየ መጻሕፍትን በመጋበዝ የንባብ ልምድና ተሞክሮአቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ:: አንባቢ ማህበረሰብን ለመገንባት በግልም ይሁን፣ በቡድን ወደ ንባብ የሚስብና ፈጠራ የተሞላበትን መንገድ በመጠቀም አብሮ ማንበብ፣ ሃሳብ መለዋወጥ እና መወያየ መድኮችን መፍጠር ያስፈልጋል::

# ነፃ ሃሳብ

## ጥብቅ አጥር ለፋይናንስ ደህንነት

**ታሪኩ ዘለቀ**

ዘመኑ የቴክኖሎጂ ነው:: የፋይናንስ ስርዓቱም በቴክኖሎጂ መመራት ከጀመረ ሰንበትበት ብሏል:: በአሁኑ ሰዓት በርካታ ነገሮች ወደ ዲጂታል እየተቀየሩ ነው:: የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች መበራከትን ተከትሎ አብዛኛው ግብይት በዲጂታል እየተሳሰረ መጥቷል::

የዲጂታል ስርዓት መስፋፋት ደግሞ አገልግሎት አሰጣጥን በማቅለል የተጠቃሚዎችን እንግልትን በመቀነስ ፋይዳው የጎላ ነው:: በተለይ የፋይናንስ አገልግሎቶች ዲጂታል መሆናቸው ደንበኞች ባሉበት ቦታ ሆነው በተንቀሳቃሽ ስልካቸው ጭምር በቀላሉ ግብይትና ክፍያ እንዲፈፅሙ በማስቻል ጊዜንም እየቆጠበ ይገኛል::

ይህም ሆኖ ቴክኖሎጂን መሰረት በማድረግ ሰዎች ትክክለኛ ማንነታቸውን ደብቀው ወንጀል በመፈፀም የተገኘውን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስለው የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ወደ ፋይናንስ ስርዓት ውስጥ ለማስገባት ጥረት ሲያደርጉ ይታያል::

ገንዘብ ሕግን በተከተለ መልኩ ሲቀመጥና የአወጣጥ ስርዓቱም ይህንኑ የተከተለ ሲሆን የፋይናንስ ደህንነቱ የተረጋገጠ ነው ማለት እንችላለን:: ከዚህ በተቃራኒው በቂ የሆነ የፋይናንስ ደህንነት መሰረተ ልማት አለመኖርና እንዲሁም ደግሞ የባንኮች የውስጥ ሰራተኞች ታማኝነት መጉደልና በሶስተኛ ወገን አማካኝነት ባንኮች የፋይናንስ ደህንነታቸው ስጋት ውስጥ ሊገባ ይችላል::

ብሄራዊ ባንክ ሚያዚያ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ይፋ ባደረገው ሪፖርት የሀገሪቱ ባንኮች በበይነ መረብ ማጭበርበሪያ ስልቶች በከፍተኛ ደረጃ እየተጋለጡ መሆናቸውን አስታውቋል:: በዚህ ምክንያትም በሀሰተኛ ሰነዶችና በሌሎች የማጭበርበር ድርጊቶች ባንኮች በአንድ ዓመት ውስጥ 1 ቢሊዮን ብር ማጣታቸውን የብሄራዊ ባንክ መረጃ ያሳያል::

ከዲጂታል ፋይናንስ ወይም ከኤሌክትሮኒክስ ፋይናንስ ጋር ተያይዞ የሚፈፀም የማጭበርበር ድርጊትን ለማቆም በዋናነት የፋይናንስ ተቋማቱ/ባንኮች የውስጣቸውንና የደንበኞቻቸውን ደህንነት ለማረጋገጥ ጥብቅ አጥር መፍጠር አለባቸው:: ይህ ካልሆነ ግን ለአደጋ እንደሚጋለጡ የዘርፉ ምሁራን ደጋግመው ሲናገሩ ይሰማል::

የባንኮች የፋይናንስ ደህንነት የተጠበቀ ካልሆነ በቅድሚያ ራሳቸው ባንኮቹ ተጎጂ ይሆናሉ:: ከዚያ መለስ ሲል ደግሞ ደንበኞችንም ሊያጡ ይችላሉ:: በዚህ ምክንያትም አንድ ባንክ ስራ እስከማቆምም ሊደርስ ይችላል:: የባንኮች አስፈላጊ ነገር መልካም ስራቸውና ዝናቸው ነው:: አንዴ ስማቸውና ዝናቸው ከጠፋ ከገበያ ወጡ እንደማለት ነው::

ቴክኖሎጂን መሰረት በማድረግ ከትንሽ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የማጭበርበር ድርጊት ድረስ ሰነድን ጨምሮ በበርካታ ሚሊዮኖች የሚቆጠር የብር ማጭበርበሮችም ይፈፀሙበታል:: ይህ ደግሞ በሀገር ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ደህንነት ላይ ዘርፈ ብዙ ችግሮችንም ያስከትላል:: ሀገሪቱን የሚያንቀሳቅሱት የገንዘብ ተቋማት የሚባሉት ባንኮች እና ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ናቸው:: እነዚህ ተቋማት በዚህ መልኩ ሀገርን እንዲያንቀሳቅሱ ደግሞ ደንበኞቻቸው የሀገሪቱ ዜጎች እንዳይከስሩና እንዳይጎዱ ጥንቃቄው የበረታ መሆን አለበት:: በማጭበርበር ምክንያት ዜጎች ሲከስሩ በሀገሪቱ ላይ የሚያመጣው ኪሳራ ከበድ ይላል::

ከአሁን በኋላ እያንዳንዱ ስልክ የያዘ ሰው ከባንኮች ጋር ግንኙነት የሚፈጥርበት ሁኔታ ተመቻችቷል:: እያንዳንዱ ሰው የባንኮች ቅርንጫፍ ሆኖ የማገልገል ተግባር የጀመረበት ወቅት ነው:: 70 ሚሊዮን የኢንተርኔት ባንኪንግ ተጠቃሚዎች ካሉ 70 ሚሊዮኖቹም ከባንኮች ጋር ስርዓት ጋር ተሰናስነዋል ማለት ነው::

> **በኢትዮጵያ የፋይናንስ ስርዓቱ ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ ዘመናዊ የአሰራር ስርዓት ተነድፎ እየተሰራ ይገኛል**

በእርግጥ ዲጂታል የገንዘብ ዝውውር ጥሬ ገንዘብን ይዞ ከመንቀሳቀስ ይልቅ ይበልጥ ምቹ እንደሆነ ታምኖበታል:: በኢትዮጵያም ባለፉት ሁለት ዓመታት እና ሶስት ዓመታት የገንዘብ ዝውውሩ ቴክኖሎጂን ተከትሎ ተግባራዊ እየተደረገ መምጣቱ ይበል የሚያሰኝ ነው:: ጠቀሜታውም የገዘፈ ነው::

መንግስት ለገንዘብ ሕትመት በየጊዜው የሚያወጣውን ከፍተኛ ገንዘብ ከማስቀረት ረገድ እንዲሁም ጥሬ ገንዘብን ይዞ መንቀሳቀስ ተገቢ አለመሆኑን የሚያስረዳ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው:: ዲጂታል የገንዘብ ዝውውር ሀገሪቱን ከዓለማቀፍ የንግድ ስርዓት ጋር ይበልጥ የሚያስተሳስራትና ኢኮኖሚውን አንድ እርምጃ የሚያሳድግ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይመሰክራሉ::

በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ የዲጂታል ግብይት ለመጀመሪያ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ በልጧል:: የፋይናንስ ስርዓቱም ወደ ዲጂታል አሰራር እየተቀየረ ነው:: የወረቀት ብር ዝውውር በእጅጉ እየቀነሰ በዲጂታል መልኩ ግብይትና ክፍያ መፈፀም እየተለመደ ነው::

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መረጃ መሰረት በ2016 ዓ.ም ግማሽ ዓመት ብቻ ከ2 ነጥብ 8 ትሪሊየን በላይ በዲጂታል የባንክ አገልግሎት ገንዘብ ማንቀሳቀስ ተችሏል:: ይህ የዲጂታል ኢኮነሚ የገንዘብ ስርዓቱን ከማዘመን አንፃር ያበረከተው ፋይዳ ከፍተኛ ተብሎለታል:: የአገልግሎቱ ፈላጊዎች ባሉበት ስፍራ ሆነው በቀላሉ ገንዘባቸውን ማንቀሳቀስ መቻላቸው ጠቀሜታውን ገዘፍ ያደርገዋል::

በኢትዮጵያ በጥሬ ገንዘብ እየተደረጉ ያሉ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች እየቀነሱ በመምጣት ላይ ናቸው:: ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የባንክ የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴን ተግባራዊ ያደረገው መመሪያ አስተዋፅኦ ተጠቃሽ ነው:: ለግለሰብ እስከ 50 ሺህ ብር ዝቅ ብሏል፣ለኩባንያዎች እስከ 1 መቶ ሺህ ብር እንዲሆን ተወስኗል::

ከዚህ በላይ ጥሬ ገንዘብ ማንቀሳቀስ ከተፈለገ ግን ዲጂታል የገንዘብ አገልግሎትን መጠቀም እንደሚገባ መመሪያው ያዛል:: ይህ ደግሞ ለጥሬ ገንዘብ ዝውውሩ መቀነስ አይነተኛ ሚና ተወጥቷል:: ገበያው ላይ፣ የግብይት ሂደትና ዝውወር ላይ ሁሉም ሰው በዲጂታል ገንዘብ ሲጠቀም በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው::

ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መረጃ እንደሚያመለክተው በሞባይል ባንኪንግ ብቻ 2 ነጥብ 4 ትሪሊዮን ብር ገንዘብ ማዘዋወር ችሏል:: በተመሳሳይ ሌሎች ባንኮችም በዲጂታል የባንክ አገልግሎት የሚያንቀሳቅሱት የገንዘብ መጠን እያሳደጉና አብዛኛው የገንዘብ እንቅስቃሴ በዚሁ የዲጂታል የባንክ አገልግሎት እያካሄዱ መሆናቸው ይታወቃል::

ታዲያ ይህን መሰል የገንዘብ ዝውውር ከዓለማቀፉ ንግድ ስርዓት ጋር የበለጠ የማቀራረብ አቅሙ ከፍተኛ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ:: ዲጂታል የባንክ አገልግሎት በዚህን ያህል ደረጃ እያደገ መምጣት ባንኮችና ሌሎች አገልግሎቱን የሚሰጡ ተቋማት ገቢ እየጨመሩ መሆኑ ይታመናል::

በዚህ ዘመናዊ የገንዘብ እንቅስቃሴ መተግበሪያዎችን የሚጠቀሙ ደንበኞች እያደገ መሄድ የገንዘብ እንቅስቃሴው እንዲጨምር እያደረገው ነው:: ቴክኖሎጂን አንድ የሕይወት አካል ማድረግ መቻሉ መንግስት ለብር ህትመት የሚያወጣውን ወጪ በመቀነሱና ለምዝበራዎች የሚውለውን ገንዘብ በስርዓት እንዲመራ ያደርገዋል::

የዲጂታል የባንክ አገልግሎት ለተገልጋዩም ሆነ ለባንኮች እጅግ ጠቃሚ መሆኑ አነጋጋሪ ጉዳይ አይደለም:: ተገልጋዩ በቀላሉ ገንዘብ በማንቀሳቀስ እና ክፍያዎችን መክፈል እያስቻለው ነው:: ይህ አሰራር ጥቅሙ ቢያመዝንም ተገቢው ጥንቃቄ ካልተደረገ ግን የፋይናንስ ተቋማትን ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ያደርጋቸዋል:: ይህን ስጋት ለመከላከልና በሳይበር ጥቃት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ ደግሞ ሀገራትም ሆኑ የፋይናንስ ተቋማት የሳይበር ደህንነታቸውን ማሻሻልና ማዕቀፍ ማበጀት እንደሚገባቸው ይመከራል::

በኢትዮጵያ የፋይናንስ ስርዓቱ ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ ዘመናዊ የአሰራር ስርዓት ተነድፎ እየተሰራ ይገኛል:: አንዳንድ ጊዜ የፋይናንስ ስርዓቱ የማጭበርበር ችግሮች ሲገጥሙት ይስተዋላል:: ባለፈው ጊዜ በንግድ ባንክ ላይ የደረሰውን ማንሳት ይቻላል:: በወቅቱ የባንኩ ፕሬዚደንት አቶ አቤ ሳኖ የደረሰውን የገንዘብ ማጭበርበር ተግባር ለመቆጣጠር በፍጥነት ለመቆጣጠር ለመገናኛ ብዙሀን መግለፃቸው ይታወሳል::

ይህ ለአብነት ያነሳነው ጉዳይ ቢሆንም የፋይናንስ የማጭበርበር ተግባር በተለይም በባንክ ስርዓቱ ላይ ትልቅ እንቅፋት እየሆነ የመጣው ሕገወጥ የሀዋላ አገልግሎት የሚጠቀስ መሆኑን የባንክ ባለሙያዎች ይናገራሉ:: ከጥቁር ገበያ ተገዝቶ ወደ ዲያስፖራ አካውንት የሚቀመጥ ገንዘብ ወንጀል ሲሆን ሶስት ወንጀሎችንም አካቶ ይዟል::

አንደኛ ሀሰተኛ የመንግስት ሰነድ ማዘጋጀት በራሱ ወንጀል ነው:: ሁለተኛ ሰነድ ማዘጋጀት ማጭበርበር ነው:: ሶስተኛ ከጥቁር ገበያ ዶላሩን ገዝቶ ወደ አካውንት ማስገባት ሌላኛው ወንጀል ነው:: የእነዚህ ድምር ውጤት ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርን የመፍጠር አቅም አለው::

በዚህ መንገድ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ጠንካራ የሆነ የምርመራ፣ የክስና ገንዘቡን የማስመለስ ስራ ቢሰራ ሌሎችን የማስተማር እድሉ ሰፊ ነው:: በቴሌ ብር፣ በሞባይል እንዲሁም በተለያዩ የማህበራዊ ትስስር ገፆችን በመጠቀም ገንዘብ የማጭበርበር ተግባራትን የሚፈፅሙ ግለሰቦችን የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በማስፋፋት፣ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓትን በመዘርጋት የፋይናንስ ደህንነትን ማስጠበቅ ግዴታ ነው::

ከዲጂታል የባንክ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በርካታ የማጭበርበር ሙከራዎች እየታዩ መምጣታቸውን ተከትሎ ይህንን ስጋት ለማስቀረት በጥንቃቄ መስራት ይገባል:: ማጭበርበሮች ሲታዩ ማህበረሰቡ እንዲያውቀውና ጥንቃቄ እንዲያደርግ መረጃዎችን በፍጥነት ማድረስ ያስፈልጋል:: የፋይናንስ ተቋማት የሚመጣው ነገር/ማጭበርበር ከመምጣቱ በፊት ሙከራ ሲደረግ ማሳወቅ አለባቸው:: ደንበኞችም አጠራጣሪ ጉዳይ ሲገጥማቸው ለገንዘብ ተቋማት ማሳወቅ ይገባቸዋል::

የፋይናንስ ዘርፉ በጥብቅ ስርዓት ካልተመራ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት ያስከትላል:: ባንኮችና መሰል የፋይናንስ ተቋማት ጥብቅ አጥር በገንዘብ ዝውውራቸው ላይ ማበጀት እንዳለባቸው የምጣኔ ሀብት ምሁራን ሲናገሩ ይደመጣል:: በቅርቡ የብሄራዊ ባንክ ባወጣው ሪፖርትም በአንድ ዓመት ብቻ 2 ቢሊዮን ብር ከባንኮች ማጭበርበር ተፈፅሟል ሲል ገልጧል:: ከባንኮችም ዶላር ሊያጭበረብሩ ሲሉ መያዛቸው ይታወቃል::

በመሆኑም ማንኛውም ተቋም ወይም ግለሰብ ዲጂታል ፋይናንስ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ ዝውውር በሚጠይቅበት ወቅት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል:: የፋይናንስ ደህንነት አስተማማኝና ደህንነቱ እንዲሆንም ብሄራዊ ባንክን ጨምሮ መንግስት ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግም ይጠበቅበታል::

ብሄራዊ ባንክ በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ንግድ ባንኮችና የመንግስት ባንኮች አግባብ ያለው የደህንነት እርምጃዎች እየወሰዱ እንደሆነ፣ ጥንቃቄዎችን እያደረጉ እንደሆነ፣ ፖሊሲዎቻቸውን በአግባቡ እየተገበሩ እንደሆነ መቆጣጠርና ኦዲት የማድረግ ኃላፊነቱ ከዚህ ቀደሙ በተሻለና ዘለቄታነት ባለው መልኩ ሊወጣ ይገባል:: የፋይናንስ ተቋማትም የአሰራር ስርዓታቸውን ደህንነት ቀልጣፋነት ይበልጥ ለማሳደግ የቴክኖሎጂ ተለዋዋጭ ባህሪን በማየት በቀጣይነት መስራት ይጠበቅባቸዋል::

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የዘርፈ ብዙ ሙያዎች ባለቤት

ክብረአብ በላቸው

ብዙዎች እንደሚሉት፤ በዚች ዓለም ውስጥ ስኬታማ ሆኖ ለመኖር ራስን ማጠናከርም ሆነ ማዳከም የሚፈጠረው በአእምሮ አጠቃቀማችን ልክ ነው:: ያለውን አቅም በአግባቡ የማይጠቀም ሰው ደካማ ነው ሊባል ይችላል። የሚሆነውንና የሚችለውን ፈልጎ የማግኘት ጉዳይ ካልሆነ በቀር በተፈጥሮ ደካማ ሆኖ የተፈጠረ ሰው የለም:: ወጣቶችም ይህን በውል መረዳት አለባቸው :: ተስፋ መሰነቅ ለወጣቶች ትልቅ ጉልበት ይሆናል:: ጉልበት የሚሆንለት ግን በዕውቀት ሲመራ ነው። አንድ ወጣት ምንም ነገር ከማድረጉ በፊት ራሱን መፈተሽ ይኖርበታል። ምንድነው የምችለው ? ምንድነው የማልችለው ? ብሎ አቅሙን መለካት አለበት::

ወጣቶች ስኬታማ ለመሆን በመጀመሪያ የራእይ ሰው መሆን እንደሚያስፈልግ ብዙዎች ያነሳሉ:: ራእይ የለሽ ሰው ካለበትና ከደረሰበት አልፎ ለመሄድ አይፈልግም :: ይህ የሚሆነው ዓይኑ የተተከለው በገሃድ በሚታየው ላይ ብቻ በመሆኑና በዓይነ ህሊናው የሚያየው እይታ ስለሌለው ነው:: ባለ ራእይ ሰው ባለበት ሳይወሰን ወደ አዲስ ነገር ለመግባት ይገሰግሳል :: ራእይ የለሽ ሰው አይነ ስጋው ብቻ የተከፈተና በፊቱ ያለውን ብቻ እንዲያይ የሚገደድ ሰው ነው:: ባለ ራእይ ሰው ግን አይነ ህሊናው የተከፈተ በመሆኑ በፊቱ ካሉት በእጁ ከጨበጣቸው እውነታዎች ባሻገር በማየት ያልማል።

ሕልም ተስፋ እና ትጋት በአንድ መንፈስ ከሄዱ መጨረሻቸው ድልና ስኬት ነው የሚባለው እንዲሁ ዚም ተብሎ አይደለም ሕልማቸውን ሰንቀው በትጋት የተራመዱ እና የስኬት ማማ ላይ የተቀመጡ ብዙዎቹ ስላሉ እንጂ። ዛሬ ስለ ስኬት ማንሳታችን ያለምክንያት አይደለም። የዚህ ሳምንት የወጣቶች አምድ እንግዳችን የዘርፈ ብዙ ሙያዎች ባለቤት ሐኪም ደራሲና ሰዓሊ የሆነው ወጣት ሚካኤል አርጋው በመሆኑ እንጂ።

ዶክተር ሚካኤል አርጋው ውልደቱ በመዲናችን አዲስ አበባ ሲሆን ቤተሰቦቹ በሥራ ምክንያት ወደ ሀዋሳ በማቅናታቸው የልጅነት ግዜውን ያሳለፈው በሀዋሳ ከተማ ነው። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በሀዋሳ ኤስ ኦ ኤስ (SOS) ትምህርት ቤት መከታተል ችሏል። በትምህርት አቀባበሉ ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል የነበረው ሚካኤል በ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ጥሩ ውጤት በማምጣት ወደ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በማቅናት በህክምና ትምህርት በዶክትሬት ድግሪ ተመርቋል። በአሁኑ ወቅትም በቡታጅራ አጠቃላይ ሆስፒታል ሀገሩን እያገለገለ ይገኛል።

አስራ ሁለተኛ ክፍል ውጤት መጥቶ የዩኒቨርሲቲ ምደባ እስኪደረግ ድረስ የሕክምና ትምህርት የመማር ከልጅነት ጀምሮ የነበረ ህልምም ሆነ ፍላጐት እንዳልነበረው የሚናገረው ዶክተር ሚካኤል፤ ከልጅነት ጀምሮ የነበረው ሕልም አርክቴክት የመሆን እንደነበር ነገር በመጨረሻ ሰዓት ከራሱና ከቤተሰቡ ጋር በመመካከር የሕክምና ትምህርት ለመከታተል ወስኖ ትምህርቱን እንደቀጠለ ይናገራል።

ዶክተር ሚካኤል የአስተዳደግ ሁኔታው ምን ይመስል እንደነበር ሲናገር፤ የሚፈልገውን ነገር ምክንያታዊ ሆኖ ማስረዳት እስከቻለ ድረስ የሚፈልገው ነገር ሁሉ እየተደረገለት እንዳደገ ይናገራል። ይህም በትምህርት ውጤታማ ሆኖ ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ በጎ ተፅዕኖ እንደነበረው ያስረዳል።

ወጣቱ ዶክተር ሚካኤል አርጋው ሕክምና ባለሙያ ብቻ አይደለም ሰዓሊ ጭምር እንጂ፤ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር በነበረው ቆይታ ሙሉ ትኩረት በሚፈልገው የሕክምና ትምህርት ዘርፍ ላይ ሆኖ የስዕል ሥራውን እንዴት መቀጠል እንደቻለ ሲናገር፤ ከልጅነት ጀምሮ በትምህርት ቤት እንደ የቤት ሥራ የሚሰጡ የስዕል ሥራዎችን እንደ ትልቅ ፕሮጀክት ወስዶ ይሰራ እንደነበር ተናግሮ፤ ነገር ግን ለስዕል ከፍተኛ ትኩረት ይሰጥ የነበረ ቢሆንም ሰዓሊ እሆናለሁ የሚል እምነት እንዳልነበረው ይገልጻል።

ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሲደርስ መሠረታዊ የስዕል ትምህርት (technical drawing) ይሰጥ ነበር የሚለው ዶክተር ሚካኤል፤ በዚህን ወቅት ለስዕል የነበረው ፍቅር ይበልጥ እንደጨመረ ይናገራል። በወቅቱ የጓደኞቹን ጨምሮ የተለያዩ የማስመሪያ ስዕሎችን በመሥራት ይሰጥ እንደነበር ይህም ለስዕል ያለው ፍቅር ይበልጥ እንዲጨምር እንዳደረገው የልጅነት ግዜውን አስታውሶ ይናገራል።




ዶክተር ሚካኤል አርጋው

> **የአዕምሮ ጤና ሲቃወስ የግለሰብ የየዕለት ተግባር፣ ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እና የሰውነት ሁኔታ ላይም ተጽዕኖ አለው**

በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት የሕክምና ትምህርት ተቋርጦ ለዘጠኝ ወራት ቤት በተቀመጠበት ወቅት በልጅነት ይሰራ የነበራቸውን የስዕል ሥራዎች ደግሞ በመጀመር የሰራቸውን የስዕል ሥራዎች በማህበራዊ ሚድያ በመጋራት ከተመልካች ባገኘው በጎ ምላሽ ያገኘው ዶክተር ሚካኤል፤ በዚህ የተመልካች አስተያየት በመነሳት የስዕል ሥራውን አጠናክሮ ስለመቀጠሉ ይናገራል።

ከዚህ በተጨማሪ ወደ ፅሑፍ ሥራው ወይም ወደ ደራሲነት ስለመጣበት አጋጣሚ ሲናገር፤ ``የሕክምና ትምህርት ብዙ ግዜ የሚወስድ ተጨማሪ ሥራ ለመሥራት የሚሆን ሰዓት የማይገኝበት ቢሆንም ከልጅነቱ ጀምሮ ሁለገብነትን በጣም ስለሚወድ በአንድ ሙያ ተገድቦ የመኖር ዓላማም ሆነ ፍላጐት አልነበረኝም የተለያዩ ነገሮችን መሞከር አዲስ ነገር ማየት ያስደስተኛል በዚህም ምክንያት አዲስ ነገር ለማወቅና ለመማር ግዜ አላጣም ነበር'' ይላል።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ከሶስተኛ ዓመት ተማሪ ከነበረበት ግዜ ጀምሮ ወደፊት ለሕትመት ይሆናሉ በሚል የተለያዩ ፅሑፎችን መፃፍ እንደጀመረ የሚናገረው ዶክተር ሚካኤል፤ መፅሐፍ እንደ መዝናኛው ሆኖ ከትምህርቱ ጎን ለጎን በማስኬድ ሥራዎቹን ከቆይታ በኋላ ለህትመት እንዳበቃቸው ይናገራል።

ዶክተር ሚካኤል በመጀመሪያ ለህትመት ስለበቃውና በሁለት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛና በእንግሊዝኛ ስለተዘጋጀው (የተሸሹ ድምጾች) ስለተሰኘው መፅሐፉ ሲናገር፤ የስነልቦና ወይም የስነ አዕምሮ ጤና ላይ ትኩረት ያደረገ ይዘት ያለው መፅሐፍ መሆኑን ገልፆ፤ በተጨማሪም የፍልስፍና ዕይታዎችን ያካተተ የልብወለድ ዓለምን የሚዘክር መፅሐፍ መሆኑን ይናገራል።

በሌላ በኩል አንድ የሕክምና ባለሙያ የራሱን ሕመም ደብቆ ወይም ችላ እያለ በየዕለቱ የስነልቦና ሕመም የገጠማቸው ሰዎች እያስተናገደ ስላለበት ሁኔታ መፅሐፉ እንደሚዳስስ የሚናገረው ዶክተር ሚካኤል፤ ይህም የሕክምና ባለሙያው የሚከፍለውን መስዋዕትነት ዋጋ ለመስጠት በማሰብ የተደረገ ስለመሆኑ ይናገራል።

ማህበራዊ ጉዳይ፣ የገቢ ሁኔታ፣ ጥሩ ያልሆኑ የልጅነት ልምዶች፣ አፈጣጠርና መሰረታዊ የጤና ሁኔታዎች የአንድን ሰው የአእምሮ ጤንነትና ስነልቦና ሁኔታ ሊወስኑ እንደሚችሉ የሚናገረው ዶክተር ሚካኤል፤ መፅሐፉ በመላው ዓለም ሆነ በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከወረርሽኝ በላይ ወጣቱን እየተፈታተነው ያለውን የስነ አዕምሮ መታወክ (mental health burden) በተመለከተ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት በመስጠት የሚተርክ እንደሆ ያስረዳል።

ዶክተር ሚካኤል እንደሚናገረው፤ የሕክምና ትምህርት ቤት ብዙ ነገር የሚታይበት ነው። በአዕምሮ ፈተና ያለበት ብዙ ወጣቶች ለተለያዩ የአዕምሮና የስነልቦና ችግሮች ሲጋለጡ የምንመለከትበት ነው። የዚህ ምክንያት የሕክምና ትምህርት ከባድ ኃላፊነት መሸከም የሚጠይቅ ስለሆነ ነው። በዚህ ሁሉ ፈተናዎች ይገጥማሉ፤ በተጨማሪም ሕመም ገጥሞት የሚመጣ ሰው ማከም ወይም ደግሞ አድምጦ ምላሽ መስጠት በራሱ የሚፈጥረው ከፍተኛ የአዕምሮ መጨናነቅ አለ፤ መፅሐፉ እነዚህን ጉዳዮች በማንሳት ትምህርት ለመስጠት የተዘጋጀ ነው ይላል።

ከዚህ በተጨማሪ የሕክምና ትምህርት ውስጥ ያሉ ወጣቶች እንደ ሌሎች ጓደኞቻቸው በመጨዋወት በተለመደው መልኩ የወጣትነት ግዜያትን ለማሰለፍ ዕድል የማይሰጥ እንደሆነ የሚናገረው ዶክተር ሚካኤል፤ በዚህ ምክንያት ብዙ የሕክምና ተማሪዎች የአዕምሮ መታወክ ውስጥ ይገባሉ ስለዚህ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ለሚያጋጥማቸው ፈተና የስነልቦና ዝግጅት እንዲያደርጉ በሚረዳ መልኩ የተዘጋጀ መፅሐፍ መሆኑን ይገልጻል።

በሌላ በኩል ወጣቱን ጨምሮ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ በተለያየ የሕይወት መስክ የተሰማሩ ግለሰቦች በስነ አዕምሮ ችግር በጣም እየተሰቃዩ እንዳለ የሚናገረው ዶክተር ሚካኤል፤ ያለ አዕምሮ ጤና የሌለ በመሆኑ ይህንን ከግምት በመውሰድ ሁሉም ሰው በአሁኑ ወቅት አንገብጋቢ ችግር ስለሆነው የአዕምሮ ጤና ግንዛቤ እንዲኖረው በማሰብ ለሕትመት እንዳበቃው ይናገራል።

ሌሎች በአካል ላይ የሚያጋጥሙ ሕመሞችን በመድሀኒት ወይም በቀዶ ሕክምና ማከም ይቻላል የሚለው ዶክተር ሚካኤል፤ የስነ አዕምሮ ችግር ግን ውስብስብና በቀላሉ የሚታከም ባለመሆኑ ቅድመ ጥንቃቄ ላይ ነው ትኩረት ማድረግ የሚያስፈልገው፤ ከዚህ አንፃር መፅሐፉ የስነልቦናና የስነ አዕምሮ ጉዳዮችን በተመለከተ በዝርዝር የሚተነትን በመሆኑ ፋይዳው ከፍተኛ እንደሆነ ይናገራል።

በአዕምሮ ጤና ቀውስ ማሻሻያ ላይ የራሱን አሻራ ለማሳረፍ በማሰብ ይህንን መፅሐፍ ለአንባቢያን ለማቅረብ እንደተነሳሳ የሚናገረው ዶክተር ሚካኤል፤ የአዕምሮ ጤና ሲቃወስ የግለሰብ የየዕለት ተግባር፣ ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እና የሰውነት ሁኔታ ላይም ተጽዕኖ አለው:: ዕድሜ፣ ጾታን፣ የገቢ ሁኔታን ወይም ዘር ሳይለይ ሁሉም ሰው ለአእምሮ ጤና መታወክ በሽታ የመጋለጥ ዕድል አለው ከዚህ ለመዳን ትክክለኛው አማራጭ ቅድመ ጥንቃቄ ነው ይላል።

የስነ አዕምሮ ተፅዕኖ በኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት በአፍላ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሰሩ ጥናቶች ያሳያሉ የሚለው ዶክተር ሚካኤል፤ ከዓለም የቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር ተያይዞ ዲጂታል ሚዲያው በአዕምሮ ጤና ላይ እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። ከዚህ አኳያ መፅሐፉ ችግሩን ለማቅለል አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ይናገራል።

ዶክተር ሚካኤል እንደሚናገረው፤ በአሁኑ ወቅት መፅሐፉ በዓለም አቀፍ ዲጂታል መገበያያ በሆነው አማዞን (Amazon) የተለያዩ ግምገማና መመዘኛዎችን አልፎ ሽያጭ ላይ ይገኛል። በዚህ ዓለም አቀፍ ከሆኑ አንባቢዎች አበረታች የሆኑ አስተያየቶች እንዳደረሱት ይናገራል።

መፅሐፉ ለሀገር ውስጥ አንባቢያን በተለያዩ አመራጮች ቀርቧል የሚለው ዶክተር ሚካኤል፤ ዲጂታል በሆነ መንገድ በፅሁፍ አፍሮድ በተሰኘ የሞባይል መተግበሪያ (Afroread mobile app) እንዲሁም በድምፅ ተራኪ በተሰኘ (Teraki Mobile app) መተግበሪያ ላይ ይገኛል። በሀገር ውስጥም ጥሩ ተቀባይነት አግኝቶ እየተነበበ እንደሚገኝ ይናገራል።

ወደፊት ይህንን መፅሐፍ ወደ ምስል በመለወጥ በፊልም የማምጣት ሀሳብ እንዳለው የሚናገረው ዶክተር ሚካኤል፤ በጥሩ ባለሙያ መፅሐፉ ወደ ፊልም ፅሑፍ ተቀይሮ ሰዎች በሚረዱት መልኩ በምስል እንዲመጣ የማድረግ ከፍተኛ ፍላጐትና እንዳለው ይገልጻል።

የሶስት ሙያዎች ባለቤት የሆነው ዶክተር ሚካኤል፤ ስለወደፊት እቅዱ ሲናገር፤ የያዛቸውን የሙያ ዘርፎች አጠናክሮ መቀጠል እንደሚፈልግ ያስረዳል። በስዕል ሙያው የራሱን የስዕል ማሳያ የመክፈት፣ በሕክምና ትምህርቱም ቢሆን በሁለት መስኮች የስፔሻሊት ትምህርት የመውሰድ፣ በድርሰቱ እንዲሁ የተለያዩ መፅሐፍትን በተለይ የአዕምሮ ጤና ላይ ያተኮሩ የፅሑፍ ሥራዎችን በስፋት የመሥራት እቅድ እንዳለው ተናግሯል።

ዶክተር ሚካኤል በመጨረሻም ለወጣቶች ባስተላለፈው መልዕክት፤ ነገ ቃል አልተገባልንም ምን እንደሚፈጠር አናውቅም መኖር ያለብን ዛሬን ነው። ስለዚህ በእያንዳንዱ አጋጣሚ ሕይወትን ቀለል አድርጎ መምራት ያስፈልጋል። ወጣቶች የስነ አዕምሮ ጤናቸውን ጉዳት ላይ ከሚጥል ነገር ራሳቸውን ማራቅ አለባቸው። በተጨማሪም ባላቸው ነገር ደስተኛ በመሆን ግዜው ላመጣው የታይታ ዓለም ባለመገዛት ኑሯቸውን መምራት እንደሚገባቸው ተናግሯል።

# በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል-በማዕድን ልማት እየታየ ያለው ለውጥ

ግርማ መንግሥቴ



አቶ ካሚል አህመድ

ከሰሩበት የማዕድን ዘርፍ አክባሪ ነው። የሰሩትን ያከብራል፤ ያስከብራልም። ትልቅ የልማት አቅም በመሆን ማገልገልም ይችላል፡፡ ማእድንን ማልማት ከተቻለ ሀገር የማእድን ውጤቶችን ከውጭ ከምታስመጣ ይልቅ በሀገር ውስጥ የማእድን ምርቶች መጠቀም፣ ምርቱን ለውጭ ገበያ በማቅረብም ይበልጥ ተጠቃሚ ልትሆን ትችላለች፡፡

በአንጻሩ በማእድኑ ካልተሰራበት ደግሞ ጠንቅ እስከመሆን ሊደርስ ይችላል፡፡ ጠላቶችን ከሩቅ ይጋብዛል። ማእድኑን በሕገወጥ መንገድ ለመጠቀም ሲሉ በሚመጡ የውጭ ኃይሎች በሚፈጠር ችግር የማእድን ሀብቱ የሚዘረፍ ከመሆኑ በተጨማሪ የሀገር ደህንነት ፈተና እስከመሆንም የሚደርስበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡ ማእድኑ በውጭ ኃይሎችና ሕገወጦች ቁጥጥር ስር እየዋለ መሄዱን ተከትሎ ባለ ማእድኖቹ ለበይ ተመልካችነት ይዳረጋሉ።

ባለ ማእድኖቹ ባለ ማእድን ላልሆኑቱ ጠባቂ፤ ውሎ አድሮም አስረካቢ ይሆናሉ። ለዚህም ነው ቱጃሩ ሮክ ፌለር የአፍሪካ ወርቅ በአግባቡ ተጠብቆ ይቆየን ዘንድ ራሳቸውን በትንሽ ሳንቲም ("እርዳታ እየሰጠን እንዳይሰሩ በማድረግ..." ማለቱ ነው) ማስጠበቅ አለብን ብሎ በተናገረው ታሪካዊ ስህተት ፈፅሞ በታሪክ ተወቃሽ ለመሆን የበቃው።

ዘላለም-አለሟን ተፈጥሮ የለገሰቻትን አንጡራ ሀብት እየተበዘበዘች ያለችው አፍሪካ ስለ መበዝበዟ ራሱ በዝባዡም የሚክደው አይደለም። ይህንን ከማረጋገጥ አኳያ፣ "በዓለም ላይ ካለው ወርቅ ግማሽ ያህሉ፤ ከአጠቃላይ በዓለም ላይ ካሉት ማእድናት አንድ ሶስተኛው የሚገኘው በአፍሪካ ነው" የሚለው የራሳቸው የፈረንጆቹ ጥናት ትክክል ሆኖ የምናገኘው ሲሆን፤ ለዚህም በ2019 ብቻ 406ቢሊዮን ዶላር ያወጣ አንድ ቢሊዮን ቶን ማዕድን ከአህጉሪቱ ለገበያ ቀርቦ የነበረ መሆኑ በቂ ማሳያ ነው።

አንድ የቅርብ ጊዜ ጥናት እንዳመላከተው፤ ከአጠቃላይ የዓለም ማእድናት 30 በመቶ፤ ከዓለም ዘይት/ነዳጅ 12 በመቶ፤ ከዓለም የተፈጥሮ ጋስ ክምችት 8 በመቶ የሚሆነው ያለው በአፍሪካ ነው።

ከዓለም የማዕድን ክምችት (global mineral reserves) አኳያ ስትመዘን አንደኛ የሆነችው አፍሪካ፤ ይህን ከፍተኛ የማእድን ክምችቷን በአይነት ስንመለከትም 92% ፕሎቲኒየም፤ 56% ኮባልት፣ 54% ከብረት ጋር ውሁድ ሆኖ የሚገኝ ኬሚካላዊ ንጥረ ነገር (manganese) እና 36% ክሮሚየም ይይዛሉ። ማእድናቱ በአውሮፓውያን እጅጉን የሚፈለጉ ሲሆን፣ በተለይ አረንጓዴ ቴክኖሎጂን ለማምረት ያላቸው አቅም ከፍተኛ በመሆኑ ከተፈላጊነታቸው አንፃር ተወዳዳሪ የላቸውም።

በተለይ የአህጉሪቱ ማእድናት ተቋም (Africa Mining IQ) ደርሼበታለሁ እንዳለው መረጃ፣ አህጉሪቱ በማዕድን ሀብቷ ምክንያት ሁሌም በውጪ ኩባንያዎች ትጎበኛለች፤ ኩባንያዎቹ ብዛታቸውና የተሰማሩበት ዘርፍ ሲታይም "776 የወርቅ፣ 180 የድንጋይ ከሰል፣ 108 ዩራኒየም ፣ 151 የአልማዝ , 113 የፕላቲኒየም እንዲሁም 89 የብረት ነክ ፕሮጀክቶች» ተብለው ሰፍረዋል፡፡ በወርቅ ፍለጋ ላይ የተሰማሩ 776 ፕሮጀክቶች ከብዛት አኳያ የመሪነቱን ስፍራ ይዘው እናገኛቸዋለን።

ስለ አጠቃላይ አፍሪካ ለመነሻ ያህል ይህን ካልን፣ ኢትዮጵያም ከፍተኛ የማዕድን መጠን ካላቸው የአህጉሪቱ ቀዳሚ አገራት ተርታ ስለ መገኘቷ ይገለጻል። ይህ የማእድን ሀብት ግን በተለያዩ ምክንያቶች እንዳለማ፣ አለመልማት ብቻም ሳይሆን በቅጡ እንዳልተጠናም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ባለፈው ዓመት (2023/5/19) አል ዐይን የተባለ ድረ-ገፅ ሚዲያ የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር አቶ ጉታ ለገሰን ዋቢ አድርጎ እንደ ዘገበው፣ ከሀገሪቱ የማእድን ሀብት እስካሁን ማወቅ የተቻለው "ከ30 እስከ 40 በመቶ የሚሆነውን ብቻ ነው፤ ሀገሪቱ እስከ 70 በመቶ የሚሆነውን የማዕድን ሀብቷን ማወቅ" አልቻለችም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ "የማዕድን ሀብት ፍለጋና ጥናት ጉዞው ደካማ መሆን፤ ፍለጋው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለመደገፉ፣ የፍለጋ ስራው ሽፋን አነስተኛ መሆኑ ሲሆን፣ የሚካሄደው ልማትም ቢሆን ስራው ባህላዊ መንገዶችን ተከትሎ መካሄዱ ነው።

የስነ-ምድር መረጃዎችን የማግኘት ችግርን ለመፍታት በጂኦሎጅካል ኢንስቲትዩት፣ በማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትና ‹‹ኦርየን አፕላይድ ሳይንስና ቴክኖሎጂ›› በተባለ ተቋም መካከል የፍለጋ ስምምነት መፈረሙን ዳይሬክተሩ አስታውሰው፣ ይህ ኦርየን አፕላይድ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የተባለው የአሜሪካ ተቋም በዋናነት በሳተላይት የተደገፈ የስነ-ምድር መረጃዎችን እንደሚያቀርብ ተናግረዋል። ስምምነቱ ማእድኑን በተለምዶ ከመፈለግ የሳተላይት ምስሎችን እየተጠቀሙ የት እንዳለ በአጭር ጊዜ መጠቆም ከተቻለ የፍለጋ ጊዜያችንን ያሳጥርልናል ይላሉ። ተዘጋጅተን ሀብቱን ቶሎ የማግኘት ፍላጎት ስላለን ለዚህ ግብዓት ይሆነናል ብለን ነው የተፈራረምነው" ብለዋል፡፡

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሥነ ምድር ትምህርት ክፍል መምህር፣ ተመራማሪ እና የትምህርት ቤቱ ዲን ምንያህል ተፈሪ (ዶ/ር) ከአሚኮ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከርሰ ምድሯ ከሦስት የአለት ዓይነቶች የተዋቀረ ነው፤ እነርሱም ኢግኒየስ፣ ሴድመንታሪ እና ሜታሞርፊክ ይባላሉ። ይህ በመሆኑም ኢትዮጵያ በርካታ የማዕድን ዓይነቶች እንደሚገኙባት ይታመናል። በሀገሪቱ በርካታ የማዕድን ዓይነቶች እንደሚኖሩ ፍንጮች እንደሚያመላክቱ ጠቅሰው፣ የት ቦታ፣ በምን ያህል መጠን ምን አለ የሚሉ ነገሮች በጥናት በውል ተለይተው እንዳልተቀመጡ ዶ/ር ምንያህል ተናግረዋል፡፡

በሀገሪቱ በማእድን ሀብታቸው በእጅጉ ከሚታወቁ ክልሎች መካከል የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አንዱ ነው፤፤ በአንድ ወቅት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ በፓርላማ ቆይታቸው ወደ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብትሄዱና ብትመለከቱ ወርቅ ሞልቷል፤ በሰፌድ ❈ ❈ ❈ ያሉለት ክልል እንደ መሆኑ መጠን አካባቢው በማእድን በኩል ሁሉ በእጁ፤ ሁሉ በደጁ ነው።

በቅርቡ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ባደረግነው ቆይታ የክልሉን የማእድን ልማት ስራ አስመልክቶ ያገኘነው መረጃም ይህንኑ አመላክቶናል፡፡ የክልሉ የማእድን ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ካሚል አህመድ በጽሕፈት ቤታቸው በተገኘንበት ወቅት በሰጡን ማብራሪያ እንዳሉትም፣ ክልሉ በማእድን ሀብት የበለፀገ ነው።

የቢሮ ኃላፊው እንደተናገሩት፤ ከአምስትና ስድስት ዓመት (ከለውጡ) በፊት የነበረው የማእድን አስተዳደርና አጠቃቀም ሁኔታ ከአሁኑ ጋር እጅጉን ይለያያል። ከለውጡ በፊት ክልሉ ማእድንን የመምራትም ሆነ ማስተዳደር መብት አልነበረውም። በተወሰኑ ሰዎች ነበር የሚዘወተረው።

የአጠቃቀም ፖሊሲም ሆነ መመሪያና ደንብ የማውጣትና ባወጣው የሕግ ማእቀፍ መሰረት የማስተዳደር ሙሉ ኃላፊነትን ክልሉ ያገኘው ከለውጡ በኋላ መሆኑን አስታውቀው፣ አሁን ክልሉ ሙሉ ለሙሉ ራሱን ችሎ፣ በራሱ እቅድ እየተመራ የማእድን ሀብቱን እያስተዳደረ፤ ለዜጎችም የስራ እድልን እየፈጠረ እንዲጠቀሙ በማድረግ ላይ ይገኛል። ለብሄራዊ ባንክም ከድሮው በተሻለ መጠን ገቢ እያደረገ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ዛሬ በክልሉ የተለያዩ ማእድናት በክልሉ አመራር ሙሉ አስተዳዳሪነት እየለሙ መሆናቸውንም ጠቅሰው፣ ወርቅ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ኳርትስ፣ ግራናይት፣ እምነበረድ እና ሌሎች ወጣቶች ተደራጅተው እየሰሩባቸው ካሉና ባለ ሀብቶች እያለሟቸው ከሚገኙት ማእድናት መካከል ናቸው ብለዋል።

‹‹በክልሉ የተደረሰባቸው፣ የታወቁና ያልተደረሰባቸው፣ ገና በጥናት ይደረስባቸዋል ተብለው ከሚጠበቁት ጋር ተዳምሮ በርካታ ማእድናት አሉ። ክልሉ በማእድን የበለፀገ ነው›› የሚሉት የማእድን ልማት ቢሮ ኃላፊው፣ ‹‹የሰላም እጦት የፈጠራቸው ውስብስብ ችግሮች እንዳሉ ሆነው፤ እነሱን በመቋቋም በዘርፉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል›› ሲሉም አስታውቀዋል፡፡

ከእነዚህ ስራዎች መካከልም አንዱና ተጠቃሹ በወርቅ ማእድኑ ዘርፍ የተሰራው መሆኑንም ገልፀዋል። ወርቅ አምራቾችን በተለያዩ ደረጃዎች በመመደብ እየተሰራ መሆኑን የሚናገሩት አቶ ካሚል፣ በግለሰብ ደረጃ በተበታተነ መልኩ ይንቀሳቀሱ የነበሩትን ወጣቶች በማደራጀትና ማህበር እንዲመሰርቱ በማድረግ በባህላዊ መንገድ በወርቅ ስራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርገዋል ይላሉ። በዚህ አሰራርም ከፍተኛ ለውጥና ውጤት ተገኝቶበታል ነው ያሉት።

እሳቸው እንዳሉት፤ ባለ ሀብቱ በዘርፉ እንዲሰማራ በማድረግ በኩልም እየተሰራ ሲሆን፣ ባለ ሀብቱ ብቻውን እንዲሰራ ከማድረግ ይልቅ የ70/30 አሰራርን በመዘርጋት ወጣቱን እንዲያሳትፍ፣ ማሽነሪዎችና ሌሎች ዘመናዊ መሳሪያዎች ከባለሀብቱ ወጣቱ በጉልበቱና ባለው እውቀት ድርሻ እንዲኖረው በማድረግ እየተሰራ ይገኛል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማእድን ዘርፉ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው የሚሉት የቢሮ ኃላፊው ይህም እያደገ በመምጣት ላይ መሆኑንም ይናገራሉ። በ2014 ዓ❈ም ሁለት ኩንታል ከ100 ግራም የነበረው ከክልሉ ወደ ብሄራዊ ባንክ የገባው የወርቅ ምርት፤ በ2015 ዓ❈ም ወደ 4 ኩንታል ከ800 ግራም አድጓል ሲሉ ገልጸዋል። ይህ የመጣው ለውጡን ተከትሎ ክልሉ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ማእድናት ላይ የማስተዳደር መብትን በመጎናፀፉ መሆኑን አመልክተው፣ የሰላም ችግር ባይኖር ኖሮ ከዚህም በላይ መስራት ይቻል እንደነበርም አስታውቀዋል።

ከማእድን ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር በተመለከተም ዋናውና ቁልፉ ችግር፣ ትልቁ ፈተና የጥቁር ገበያ ጉዳይ መሆኑን የቢሮ ኃላፊው አመልክተዋል። እንደ ኃላፊው ገለፃ፣ በርካታ ኪሎ ግራም ወርቅ በጥቁር ገበያው በኩል ይወጣል። ጥቁር ገበያው ከመንግስት በከፍተኛ ደረጃ የዋጋ ልዩነት ስላለው ወርቅ አምራቾቹ ወደዛ የመሄድ አዝማሚያ ያሳያሉ። ይህ በከፍተኛ ደረጃ ችግር እየሆነ ነው። በተለይ ችግሩን የከፋ የሚያደርገው የማዘዋወር ፍቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ይህንን ስራ እየሰሩ መሆናቸው ነው፡፡

አቶ ካሚል በክልሉ በጥቁር ገበያው ተሰማርተው ከተገኙ 10 ሕገወጦች መካከል 8ቱ የማዘዋወር ፍቃድ ያላቸው ናቸው ሲሉም ጠቅሰው፣ ይህን ችግር በክልል ደረጃ ለመቆጣጠርና ስርአት ለማስያዝ እየተሞከረ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ፈቃድ ከማገድ ጀምሮ ማስጠንቀቂያ መስጠት ድረስ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል ብለዋል።

በማእድን ልማቱ ዘርፍ ሊቀረፉ የሚገባቸው ሌሎች ችግሮች እንዳሉም ጠቁመው፣ በክልሉ ማእድንን ለማልማት የሚያስችል ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለመኖር አንድ ችግር መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ እስከ 30 ሜትር ድረስ በባህላዊ አሰራር እየተቆፈረ ማእድን እንደሚወጣ ገልጸዋል፡፡

ማእድን አምራቾቹ ለማጠቢያ የሚጠቀሙበት ኬሚካል (የሜርኩሪ ዝርያ) በጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑንም ጠቅሰው፣ ዘርፉ በተሟላ እውቀት አለመመራቱና የመሳሰሉት ችግሮች የዘርፉ ፈተናዎች መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ለሚደረገው ጥረት በፌዴራል ደረጃ በዘርፉ የሚንቀሳቀሱ አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉም ጠይቀዋል። የማእድን አጠቃቀም መመራት ያለበት ምን ጊዜም በሕግና በሕግ ብቻ መሆን እንዳለበትም አስገንዝበዋል፡፡

ከዚሁ ከማእድን ልማትና ምርት ጋር በተያያዘ አምቡዱሪዩ ወረዳ፣ ሆዴ ቀበሌ ወደሚገኘው ወርቅ ማምረቻ በመሄድ የአብዱልባስጥ ወርቅ አዘዋዋሪ ማህበር ስራ አስኪያጅ አቶ አልበይድ ሆጀሌን በፅህፈት ቤታቸው አግኝተን አነጋግረናቸዋል፡፡ እሳቸውም ዘርፉ አዋጭ እንደሆነ፤ ለበርካቶች የስራ እድል የፈጠረ ስለመሆኑ ጠቅሰው፣ በሚያገኙት ገንዘብ ማህበራቸውን ከማጠናከርም አልፈው ለወደፊት የቱሪስት መስህብ ሊሆን የሚችል መናፈሻ (የአምቡዱሪዩ ልዩ አነስተኛ የወርቅ አምራች ድርጅት መናፈሻ) እየገነቡ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡ ለመናፈሻው አገልግሎት የሚውሉ የዱር እንስሳትንም እያላመዱ ስለ መሆናቸው ገልጸው፤ በክልሉ የከተማ ልማት ስራዎች ላይ እየተሳተፉ እንደሚገኙ ተናግረዋል። አንዳንድ ችግሮች፣ ለምሳሌ ማጠቢያ ማሽን፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በማቅረብ የሚያግዛቸው አካል ካለ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ጠይቀዋል።

ቀደም ሲል በተሳሳተ ግንዛቤ ወደ ጫካ በመግባትና ከጸረ ሰላም ቡድኖች ጋር በመቀላቀል የራሱን ሕዝብ ሲጎዳ እንደነበረ የሚናገረው ወጣት በሽር አሸሪፍ፤ በክልሉ መንግስት የተደረገውን የሰላም ጥሪ በመቀበል፤ ወደ ሰላማዊ ኑሮ ተመልሶ በመደራጀት በስፍራው በባህላዊ ወርቅ ማንጠር ስራ ላይ መሰማራቱን ነግሮናል፡፡ የክልሉ መንግስት እነሱን በዚህ መልኩ በማደራጀት ወደ ስራው እንዲገቡ በማድረጉ ደስተኛ መሆኑን አመልክቶ፣ ዛሬ ከራሱም አልፎ ለቤተሰቦቹ ሳይቀር ቤት በመስራት ከስራው በሚገባ ተጠቃሚ በመሆን ላይ እንደሚገኝ አስታወቋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ወለፈንዲ

እዩኤል ወርቁ

በተወለድኩ በአርባኛው ዓመት በሠላሳኛው ቀን ለዘመናት ካሸለብኩበት ሞት አከል እንቅልፍ የመጀመሪያውን መንቃት ነቃሁ:: በዚህች መከረኛ ምድር ላይ እንደ ሲራራ ነጋዴ አርባ ዘመን ስመላለስ ህሊና የሚባለውን ብልት ለምን ፋይዳ አውለው እንደነበር ባላውቅም ያን ጊዜ ግን የእናቱ ማህፀን ውስጥ ተኝቶ እንደሚቃዥ የስምንት ወር ፅንስ ረፍት አሳጥቶ የሚያንፈራግጠኝ አዲስ ሃሳብ ወደ አዕምሮዬ አፀድ ገባ::

በሠው ሰራሽ ቁስ እና ሕይወት ተከብቤ በህልቁ መካከል ብቸኝነት ጥላውን ጣለብኝ:: ጭው ያለ በርሃ ውስጥ የተገኘሁ ብቸኛ እሾሃማ ተክል የሆንኩ ያህል ወፍ ዘራሽነት ተሰማኝ:: በምድሩ ላይ አንድ ስንኳን ለምለምና ርጥብ ሕይወት የሌለበት ዘላለማዊ ሀሩር:: ዙሪያ ገባየን ቃኘሁ፤ በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን ቢሄዱት የማያልቅ ምዕራፍ አልባ መንገድ እስከ አፅናፍ ተዘርግቷል:: ከተማው እጅግ ሰፊ እና ጥልቅ የአሸዋ ባህር ይመስላል:: ሰማዩ ሩቅ ነው:: መሬቱ እንደ ጥንት ግሪክ የሙታን ሀገር ሄዲዝ ስምጥ ነው:: ዓይኔን ሩቅ በላከኩት ቁጥር በግራም ሆነ በቀኝ የሚታየኝ አድማሱ ላይ የተበተነ እንደ መስታወት የሚያጥበረብር የብርሃን ፍህም ብቻ ነው:: ተራሮችና ዛፎች፣ ወንዞች እና ሸለቆዎች፣ ወፎች እና ለምለም ሳሮች፣ ሀገሮች እና ድንበሮች፣ ውሾችም ሰዎችም የሉም:: የምኖራትን ሕይወት ይህን በመሰለ የመጀመሪያው ‹‹ለምን›› ጠየቅኩ::

**ስምን ወደዚህች ምድር መጣሁ?**

በተወለድኩ በአርባኛው አመት በስድሳኛው ቀን ይኸው የብቸኝነት ስሜት ተመልሶ ጎበኘኝ:: እንደ ዘበት ጥቅጥቅ ያለ የሠው ልጆች ጫካ ውስጥ ተጥያለሁ:: እንስሳትም ሆኑ እፅዋት፣ ወንዞችም ሆኑ ሸለቆዎች፣ ተራሮችም ሆኑ ሜዳዎች፣ ውሾችም ሰዎችም አሉ:: ነገር ግን ዙሪያየን ከቦኝ እንደሚራወጠው ፍጡር ስበር፣ ስፈጥን ቆየሁና አንድ ቦታ ላይ ደርሼ ድንገት ለዘመናት ካሸለበበት እንቅልፉ የነቃው ህሊናየ ወዴት እንደምሄድ ሲጠይቀኝ መልስ በማጣቴ እግሮቼ መሬት ላይ ተቸንክረው ቀሩ:: ወደ ፊትም ሆነ ወደ ኋላ መንቀሳቀስ አልሆንልህ አለኝ:: በቆምኩበት እያለፈኝ የሚወጣውን እና የሚወርደውን የሠው ጎርፍ ተመለከትኩ:: ይሄ ሁሉ ፍጡር ከየት መጣ? ወዴትስ ነው የሚሄደው? ይተያያል እንጂ አይተያይም፣ ይነጋገራል እንጂ አይነጋገርም፣ ይስቃል ግን አይስቅም፣ ቢያለቅስም አያለቅስም:: ብቻ ይቸኩላል - ይፈጥናል - ይጣደፋል:: ወዴት? ምን ለማግኘት?

**ምንም!**

ከየት እና ምን ሊፈይድ እንደመጣ፣ ወዴትስ እንደሚሄድ የማያውቅ የሠው ልጅ ሕይወት እዚያ ከመንገዱ ዳር በሰላም ተኝተው እንቅልፋቸውን ከሚለጠልጡት የጎዳና ውሾች ሕይወት በምን ተለይቶ ሠው ራሱን ክቡር ፍጡር ነኝ አለ? የሠው ነፍስ ከትንኝ እና ከአባጨጓሬ ነፍስ ትረዝማለች ወይስ ትወፍራለችን?

በተወለድኩ በአርባኛው ዓመት በመቶኛው ቀን ህሊናየን ያስጨነቀውን እና አብዝቶ የሚፈታተነውን ጥያቄ ለመመለስ ወደ ቤተ-መቅደስ አመራሁ:: በዚያም ጥምጥማቸው እንደ ደመና የተቆለለ አንድ ዓይና ቄስ እድሜየን ሙሉ ስሰማው የኖርኩትና ያን ጊዜ ግን በተለየ ተመስጦአና ምርምር ያዳመጥኩትን ትምህርት ሲሰጡ ተደመምኩ::

የሠው ልጅ ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ይነሳል:: መላዕክትም ከስጋው የተለየች ነፍሱን በመንፈሳዊ ውትድርና ደንብ አጅበው ወደ ፈጣሪ ያቀርቧታል:: በዚያም ከራሱ ፍላጎት እና እውቅና ውጭ በተጣለባት ምድር በኖረበት ዘመን ሁሉ የፈፀመው ታይቶ ፍርድ ይሰጠዋል:: ፍርዱም ወደ ዘላለማዊ የሲኦል እሳት፣ አልያም ዘላለማዊ ምስጋና ወደሚፈስበት መንግሥተ ሰማይ መጣል ነው::

**የገሃነም እሳት ዘላለማዊ ቅጣት ይሁን፤**
**ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! እያሉ ዘላለማዊ ምስጋና**
**ሲሰው መኖርስ የማያልቅ ባርነት አይደለምን?**

የሰማሁትን ትምህርት መልሼ እየጠየቅኩና እያሰላሰልኩ ወደ ማደሪያየ ገባሁ:: እውን ገነትም ሆነ ሲኦል የሠው ልጆች ዘላለማዊ ቤት ሊሆኑ የሚገባቸው ናቸው? ነገር ግን ፈጣሪ የነገሩትን የማይረሳ፣ የጠየቁትን የማይነሳ ደግ አምላክ ነውና እኔም የምጠይቀውን አይነሳኝም የሚል ርግጠኝነት ወደ ህሊናየ ገባ:: ያን ጊዜ የሰማይና የምድር ጌታ የሆነውን ደግ አምላክ የሚከተለውን ውለታ ጠየቅኩት...

ጌታ ሆይ ነፍሴን ባርካት:: ስትባርካት ግን ከገነትም ከሲኦልም መሆን ለኔ መልካም አይደለምና ከሞትኩ በኋላ እንደ እሪያ በዚያው እንድቀርና ትንሳኤን እንዳልቀምሳት ፍቀድልኝ::

በዚያው ምሽት የመንደሬ ሰዎች ከተሰቀልኩበት ገመድ ላይ አንስተው በታላቅ አጀብ ቀበሩኝ::

ነገር ግን ይህ እግዚዓብሄር የሚሉት አምላክ የለመኑትን የማይነሳ፣ የነገሩትን የማይረሳ ሳይሆን ቀርቶ እነሆኝ የትንሳኤን ብርሃን አይቼ በመንግሥተ-ሰማይ እገኛለሁ::

በዚህ ወንዙ ወተት ያፈሳል፣ ገራም እንስሳትም፣ ክፉ አውሬዎችም ከሠው ልጆች ጋር ባንድነት እና በወዳጅነት ይኖራሉ፣ ሠዎች አይጋቡም አይዋለዱም፣ የገነትን አፀድ አጥረው የበቀሉት እፅዋትና ፅጌያት መልካም ፍሬን ያፈራሉ:: ሽቶ መዓዛን ይረጫሉ:: ፅርሃ አርያም ሰርክ በምስጋና ጠበል ትታጠባለች:: በዚህ ለህልውና ሲባል መጠፋፋት እና መገዳደል የለም:: ተኩላ እና በግ አብረው የጠዋት ፀሃይ ይሞቃሉ፣ አንበሳ እና ሚዳቋ ዘወትር የማይተጣጡ ጥብቅ ወዳጅ ናቸው:: ጅብ ከአህያ ጋር ቆሞ በምስጋና ይዘምራል:: የሠው ልጆች ህፃናት የአንበሶችን ጋማ ያበጥራሉ፣ የአናብርትን ጥፍር ይቆርጣሉ፣ በመላዕክት አክናፍ ላይ ይፈነጫሉ:: በዚህ እፅዋት የራሳቸው ሕይወት አላቸው እንጂ ለሠው ልጆችም ሆነ ለእንስሳት ደስታ እና ህልውና ሲባል መስዋዕት አይሆኑም:: ወይን እና ትርንጎዎች አይቀጠፉም፣ አደይ አበባ ከስሯ ተነቅላ የልጆች መጫወቻ አትሆንም:: በዚህ ለታቦት ተብሎ የሚቆረጥ የግራር ዘር የለም:: የዋንዛ እና የፅድ ዛፎች የገነት ቅፅር ጠባቂ ዘቦች እንጂ አልጋዎች እና ዱካዎች አይደሉም:: ዋርካዎች እና ዝግባዎች የጌታ መንበር መቀመጫዎች ናቸው::

ነገር ግን ቀን አይመሽም፣ ሌት አይነጋም:: በልግ አይበልግም፣ ክረምትም በዝናም አይረሰርስም፣ ፀሃይ እና ጨረቃ አይፈራረቁም፣ የሠው ልጅ በዚህም የሚደክምለት፣ የሚወጣ የሚወርድለት አንዳች ዓላማ የለውም:: ሕይወት በገነት ሰርክ ውሎ የማደር፤ ዘላለማዊ የምስጋና ድግግሞሽ ነው:: ውሃን ከመንፈስ ባህር እየቀዳ፣ ምግብን ከመለኮት ቃል እየሰዋ ብቻ ይኖራል:: በዚህ የተገኙ ፍጡራን ሁሉ እድሜያቸው ህልቆ መሳፍርት የለውም:: ርጉዝ ደመናዎች በአየሩ ላይ ሲንሳፈፉ አይታዩም:: የቀን ሐሩርና የሌሊት ቁር አይፈራረቁም:: ፈጣሪ ብቻ በዙፋኑ ላይ ነጭ የብርሃን ሸማ ተጎናፅፎ ያለ ማቋረጥ ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ! እየተባለ የሚሰዋለትን ዘላለማዊ ምስጋና በለበጣ እየፈገገ ያዳምጣል::

የሆነው ሁሉ ሆኖ ከሁሉም በላይ በዚህ አንድ አስከፊ ሕግ አለ:: የሠው ልጅ ሕይወት ብትሰለቸው፣ ሰርክ ዕለት ወተት የሚያፈሰው የገነት ወንዝ ሬት ሆኖ ቢመረግገው፣ የእፅዋቱ እና ፅጌያቱ ጠረን ቢሰነፍጠው፣ የምስጋና ዘላለማዊ ድግግሞሽ አቅሉን አስቶ ቢያሳብደው፣ በዚህ የመፈጠሩን አንድ ምክንያት እና የሚኖርበትን ዓላማ ፈልጎ ቢያጣ፣ ምድራዊ ሕይወቱን በገዛ ጉልበትና ሥልጣኑ አልያም በተፈጥሮ ፍቃድ እንደሚደመድም ሁሉ ሰማያዊውን ወለፈንዲ ዓለም አልፎ መሄድ ቢያሰኘው ራሱን ሰቅሎ የመግደል ፍቃድ የለውም::

**ሞትን ፈልጌ አጣሁት!**

# ዓለም አቀፍ

## በፋይናንስ ውሳኔዎች የታጀበው የሩሲያና የዩክሬን ጦርነት




ሩሲያ የዶላር እና ዩሮ ግብይትን አገግዳለች። የአውሮፓ ህብረት በበኩሉ የሩሲያን ሶስተኛ ዓመቱ ላይ የሚገኘው የዩክሬን- ሩሲያ ጦርነት አሁንም እንደቀጠለ ሲሆን አሜሪካ በሩሲያ ላይ አዲስ ማዕቀቦችን ጥላለች::

የሩሲያ ባንኮች ላይ ያነጣጠረው አዲሱ የአሜሪካ ማዕቀብ ሞስኮ ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላትን የውጭ ንግድ ለመጉዳት ያለመ እደሆነ ሮይተርስ ዘግቧል::

የሩሲያ ምርት ገበያም በዶላር እና ዩሮ የሚደረጉ ግብይቶችን ላለማካሄድ መወሰኑን የገለጸ ሲሆን ከሁለቱ ውጪ በሌሎች መገበያያ ገንዘቦች ግን ማገበያየቱን እንደሚቀጥል አስታውቋል::

ሩሲያ ከዩክሬን ጦርነት በኋላ የመገበያያ ገንዘቧን ከዶላር እና ዩሮ ጥገኝነት የማላቀቅ እርምጃዎችን ስትወስድ ቆይታለች::

ሩሲያ ካደረገቻቸው የንግድ ልውውጦች ውስጥ 53 በመቶውን በቻይና ዩዋን ያደረገች ሲሆን ቀሪው ደግሞ ዶላርን ጨምሮ ዩሮ እና የሌሎች ሀገራት መገበያያ ገንዘብ አድርጋለች::

አዲሱ የአሜሪካ ማዕቀብ የቻይናውን ዩዋን ተፈላጊነት ከፍ በማድረግ ለቤጂንግ ጥቅም የሚያስገኝ ሲሆን የሩሲያው ሩብል ደግሞ የዋጋ መቀነስ ሊያጋጥመው እንደሚችል ተገምቷል::

የሩሲያ ምርት ገበያ ባወጣው መግለጫ አሜሪካ የኢኮኖሚ ማዕቀብ ልትጥል እንደምትችል ይጠበቅ ነበር ያለ ሲሆን ለዚህም ሲባል ከተለያዩ ሀገራት ጋር አስቀድሞ የንግድ ልውውጥ በማድረግ ላይ መሆኑን አስታውቋል::

የቡድን ሰባት ሀገራት መሪዎች ጉባዔ በበኩሉ በጣልያን ባካሄደው ስብሰባ በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት የታገዱ የሩሲያ ንብረቶችን ማስያዣ በማድረግ ለዩክሬን 50 ቢሊዮን ዶላር ብድር ለመስጠት ወስኗል።

የቡድን 7 አባል ሀገራት ሩስያ በአሜሪካ እና በአውሮፓ ካላት እንዳይንቀሳቀስ ከታገደው ገንዘብ 50 ቢሊዮን ዶላር ለዩክሬን በብድር መልክ እንዲሰጥ ነው የወሰኑት።

በጣሊያን በተደረገው ጉባዔ ውሳኔውን ያሳለፉት አባላቱ የሩስያ ማዕከላዊ ባንክ በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት ያስቀመጠው 300 ቢሊዮን ዶላር ካስገኘው ወለድ ላይ ነው ገንዘቡ ለኬቭ እንዲሰጣት ሲሉ አቅጣጫ ያስቀመጡት::

በገንዘቡ አሰጣጥ ዙርያ ዝርዝር ጉዳዮች ባይጠናቀቁም እስከ ፈረንጆቹ አመት መጨረሻ ድረስ ለዩክሬን ገቢ እንደሚደረግ ተነግሯል::

ሞስኮ ከኬቭ ጋር በገባችው ጦርነት ሳቢያ በአውሮፓ ሀገራት የሚገኘው ገንዘብ እንዳይንቀሳቀስ በአሜሪካ እግድ ወጥቶበታል:: ጦርነቱ በዩክሬን ላይ ያደረሰውን ጉዳት ለመቋቋም እና ለመልሶ ግንባታ ከሩስያ ገንዘብ ወጪ መደረግ አለበት በሚለው ጉዳይ ህጋዊ አካሄድ ላይ የአውሮፓ ሀገራት እና የአሜሪካ የሕግ አዋቂዎች ለአንድ አመት ያክል ሲመካከሩ ቆይተዋል::

ገንዘቡ እንዳይንቀሳቀስ ቢታገድም ንብረትነቱ የሞስኮ ማዕከላዊ ባንክ በመሆኑ በምን አይነት መንገድ ዩክሬን ከዚህ ገንዘብ ልትጠቀም ትችላለች የሚለው ጉዳይ ሲያወዛግብ ቆይቷል::

የአሜሪካ ብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ጃክ ሱሊቫኒ ገንዘቡ ለዩክሬን መልሶ ግንባታ ፣ ለሃይል አቅርቦት ፣ ለኢኮኖሚ ድጎማ እና ለሌሎችም አስፈላጊ መንግሥታዊ ወጪዎች ይውል ዘንድ የሚሰጥ ነው ብለዋል::

የዩክሬን ባለሥልጣናት በበኩላቸው ለምሽግ ግንባታ የተመደበ 500 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ መዝብረዋል መባላቸው ተሰምቷል። የዩክሬን ሕግ አስከባሪ አካላት ከጉዳዩ ጋር በተገናኘ 30 መዝገቦችን በማጣራት ላይ እንደሚገኙ የሀገሪቱ ፓርላማ አባል ሚካኤል ቦንዳር ተናግረዋል::

የዩክሬን ፓርላማ አጣሪ ኮሚቴ ጠፋ በተባለው ገንዘብ ምክንያት በቂ የመከላከያ ምሽጎች ባለመገንባታቸው የሩሲያ ጦር ወደ ፊት እንዲገሰግስ እድል ፈጥሯል ያለ ሲሆን ገንዘቡ በሲቪል እና ወታደራዊ አመራሮች ስለመመዝበሩ ፍንጮች ማገኘቱን አስታውቋል::

ኮሚቴው የሀገሪቱ የመከላከያ ሚኒስቴር ለወታደራዊ ግንባታ የተመደበ በጀት አጠቃቀምን የተመለከተ አስቸኳይ ሪፖርት እንዲያቀርብለትም ጠይቋል:: የዓለም ባንክ በቅርቡ ባወጣው ሪፖርት ዩክሬንን መልሶ ለመገንባት በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ከ486 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንደሚያስፈልግ አመላክቷል::

በጣልያኗ ፋሳኖ ከተማ እየተካሄደ በሚገኘው ዓመታዊው የቡድን 7 ጉባዔ ለዩክሬን ተጨማሪ ድጋፍ በሚደረግበት ሁኔታ እንዲሁም በቻይና ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ “ተስፋፊነት” ላይ ትኩረቱን አድርጎ ይመክራል ተብሏል::

ሰውሰራሽ አስተውሎት ፣ የሕገወጥ ስደተኞች ጉዳይ እና የመካከለኛው ምስራቅ የጋዛ ጦርነት ተጨማሪ አጀንዳዎች ሆነው ቀርበዋል::

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ጉማ- ፍትህ የሚገኝበት፤ ቂም በቀል የሚሻርበት ስርዓት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የኦሮሞ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ የሚመራበትና የሚተዳደርበት ቱባ ባህል፣ ልምድ፣ ወግና ታሪክ ያለው ሕዝብ ነው:: በኑሮ ሂደትም እነዚህ ሲጠቀምባቸውና ሕይወቱን ሲመራበት የቆየው ባህልና ልምድ በማስቀጠሉ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሸጋገሩ አሁንም ድረስ እንደተጠበቁ ቀጥለው አንዳንዱ አካባቢዎች እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ::

የኦሮሞ ሕዝብ የሚያጋጥሙትን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት ሲመራበትና ሲተዳደርበት ከቆዩ ሥርዓቶች ውስጥ የገዳ ሥርዓት በዋነኝነት የሚጠቀስ ነው:: በሌላ መልኩም ግጭት ሲገጥመው የሚፈታበት የራሱ የሆነ የግጭት አፈታት ሥርዓት አበጅቶ አሁንም ድረስ እየተጠቀመበት ስለመሆኑ የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ::

ማኅበረሰቡ እየተጠቀመባቸው ካሉ ቱባ ባኅሎችና በጎ ልምዶች መካከል የግጭት አፈታት ስርዓት ተጠቃሽ ነው:: ይህንን ስርዓትም ግጭቶች ሲፈጠሩ ለመፍታት እየተጠቀመበት ኖሯል፤ አሁን ድረስ እየተጠቀመበት ይገኛል:: ይህ የግጭት አፈታት ሥርዓትም የሰውን ነፍስ ያጠፋ ወይም ሰው የገደለ ሰው የሚቀጣበት ሲሆን፤ ለሟችና ለወገኖች ደግሞ ፍትሕ የሚረጋገጥበትና ፍትሕ አግኝተው ካሳ እንዲካሱ የሚያደርግበት የእርቅ ሥርዓት የጉማ ሥርዓት አንዱና ዋነኛ ባሕል ነው::

የጉማ ሥርዓት የኦሮሞ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ እየተጠቀመበት የመጣ የእርቅ ሥርዓት ቢሆንም በጊዜ ሂደት የተለያዩ የመንግሥታትና የሥርዓት ለውጦች ወቅት በተፈጠረ ጫና የተነሳ እየደበዘዘና እየተዳከመ ቢመጣም ‹‹ሳይቃጠል በቅጠል›› ማኅበረሰቡ ስርዓቱ እንዲቀጥልና ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር አድርጓል:: የጉማ ሥርዓት በማኅበረሰቡ የአኗኗር ሂደት ውስጥ የሰላምና የእርቅ መሰረት ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል:: በተለያዩ ምክንያቶች በሰዎች መካከል በሚፈጠር አለመግባባት እና መጎዳዳት ሲኖር ወይም ሲፈጠር ሰላምና እርቅ ለማውረድ ጉማ ሥርዓት ትልቅ ሚና ሲጫወት የቆየና አሁንም ድረስ እየተሰራበት የሚገኝ ነው::

የጉማ ማውጣት ሂደቱም በሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት የሚፈጸም ሲሆን የሀገር ሽማግሌዎች በተጎዳዱ አካላት መካከል ጣልቃ በመግባት ጉዳዩ በሽምግልና በመያዝ በእርቅ እንዲፈታ መፍትሔ የሚያደርጉበት ሂደት ያለው ነው:: በዚህም ሂደት የሰው ነፍስ ያጠፋ (የቀጠፈ) ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ ሰው ለተበዳይ እንዲከፈል (እንዲሰጥ) የተወሰነበት ካሣ ጉማ ተብሎ ይጠራል::

ጉማ የግጭት አፈታት ሥርዓት ካሳን በመክፈል የሚያደርግ እርቅ ነው:: ይህም በዘፈቀደ የሚፈጸም ሳይሆን በተፈጠረው ግጭት ምክንያት ለጠፋው የሰው ሕይወትና ለደረሰው ጉዳት ወይም የንብረት ውድመት የሚፈጸም ራሱን የቻለ ሥርዓት አለው:: የእርቁና የጉማ ሂደቱን በሀገር ሽማግሌ የሚመራ ሲሆን ማኅበረሰቡ የተቀበለውን የአካሄድ ሥርዓት ተከትሎ የሚፈጸም ነው::

ጉማ በጊዜ ሂደት ውስጥ እያደገ መጥቶ ከፍተኛ ሀብትና ንብረት ይያዝ እንጂ መነሻው ግን በእርቁ ዕለት ለሁለቱ ወገኖች ማለትም ለገዳይና ለሟች ወገኖች ለመብል የሚከፋፈል ወይም የሚሰጥ ሥጋ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ:: ይህም የሆነበት ምክንያት ሁለቱ ወገኖች የሚፈጸሙት እርቅ ከልባቸው እንደተቀበሉት ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው::

ጉማ ሥርዓት የሚፈጸመው የሰው ሕይወት ሲጠፋና የአካል ጉዳት ሲደርስ ብቻ ሳይሆን ንብረት ላይም ጉዳት ሲደርስ እንደየደረጃው ታይቶ ተግባራዊ ይደረጋል:: ጉማ ለመክፈል ሥርዓቱ የሚያወቁ የሀገር ሽማግሌዎችና አባገዳዎች በጋራ ሆነው ግድያውን የተፈጸመበት ሁኔታ ካጣሩ በኋላ የችግሩን አስከፊነት የተመለከቱ ደረጃዎችን ያወጣሉ:: እንዲሁም የተፈጸመው የአካል ጉዳት ከሆነም በተመሳሳይ ሁኔታ የማጣራት ሥራ በመስራት ጉዳቱን አይነት በየደረጃዎች የሚያስቀምጡበት ሁኔታ አለ::

ጉማ የግጭት አፈታት ሥርዓት ካሳን በመክፈል የሚያደርግ እርቅ ነው፡፡ ይህም በዘፈቀደ የሚፈጸም ሳይሆን በተፈጠረው ግጭት ምክንያት ለጠፋው የሰው ሕይወትና ለደረሰው ጉዳት ወይም የንብረት ውድመት የሚፈጸም ራሱን የቻለ ሥርዓት አለው

ችግሩ ከተፈጸመ በኋላ በሁለቱም ወገኖች በቂምና በቀል ተነሳስተው ሌላ የሰው ሕይወት እንዳይጠፋና ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ በማሰብ ነፍስ ያጠፋው ሰው (የገዳይ ወገኖች) ለተወሰነ ጊዜ ከአካባቢው እንዲሰወሩ (እንዲርቁ) በማድረግ መረጋጋት እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ:: የሰው ሕይወት ያጠፋው ሰው (ገዳዩ) ደግሞ ወደ ማረሚያ ቤት እንዲገባ ይደረጋል:: አልፎ አልፎም ገዳዩ ወደ ማረሚያ ቤት ያልገባ ከሆነ ግን ሩቅ ወዳሉ ዘመዶቹ ዘንድ በመሄድ የሚደበቅበት ሁኔታዎች ይኖራሉ::

የሟች ወገኖች ወዲያውኑ የሀገር ሽማግሌዎችና አባገዳዎች ዘንድ በመሄድ ስለጠፋው የሰው ሕይወት የሟች ወገኖችን የሚማጸኑበት ሂደት ይፈጸማሉ:: ሂደቱም እንደየሁኔታ በአጭር ጊዜና በረጅም ጊዜ የሚቆይ ሊሆን ይችላል::

የጉማ ሥርዓት የሰው ነፍስ ያጠፋ ሰው ምክንያት የሚያጣራበት ሥርዓት አለው:: ይህም በተለያዩ መንገዶች ይፈጸማል:: ሆን ብሎ አውቆና አስቦበት የሰው ነፍስ ያጠፋ እና ሳይሰብ በድንገት የሰው ነፍስ ያጠፋ በሚል ተከፋፍሎ በተለያየ መንገድ ማጣራቶች ይደረጋሉ:: በተጨማሪም የሰው ነፍስ ያጠፋ ሰው ማጥፋቱን ያመነና ያላመነ መሆኑን የሚለይበት ነው:: ገዳይ ሆንብሎ አውቆና አስቦበት የሰው ነፍስ ያጠፋ እንደሆነ ተጣርቶ ቅጣቱ በዚያው ልክ ከፍ እንዲል ተደርጎ ውሳኔ ይወሰንበታል:: ሳያስብበት በድንገት የፈጸመው እንደሆነ ደግሞ የፈጸመውን በደል ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደጥፋቱ መጠን ቅጣት ይሆናል::

በጉማ ሥርዓት የሟች ወገኖች ያጡት ወገናቸውን በማሰብ እርቁን አልቀበልም ማለት አይችሉም:: በእርቅ ሥርዓቱ ወቅት የሟች ወገኖች እርቁን ለመቀበል እምቢ በማለት ምክንያቶችን ቢደረድሩም ፍጽም ተቀባይነት አያገኙም:: ምክንያቱም እርቅ እምቢ ማለት ማህበረሰቡ በተስማማበት የእርቅ ሥርዓት አለመመራትና አለመተዳደር ከመሆኑ ባሻገር በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚያስወግዝና እርግማን የሚያስከትል ድርጊት ነው:: የተበዳይ ወገን አሻፈረኝ እርቁን አልቀበልም እምቢ የሚል ከሆነ ስለሚረገም ይህ እርግማን ደግሞ የተወለደው እንዳያድግ፣ የተዘራው እንዳይበቅል ያደርጋል ተብሎ በማኅበረሰቡ ይታመናል:: በመሆኑም እርቁን መቀበል እንደ ግዴታ ተደርጎ ይቆጠራል::

በሁለቱ ወገኖች መካካል እርቅ ከተፈጸመ በኋላ የሚከፈለው ጉማ አይነትም እንዲሁ የተለያየ ሊሆን ይችላል:: በጉማ በዋናነት የገንዘብና የከብት ካሳ ይከፈላል (ይሰጣል):: ይህም ካሳ ለሟች ቤተሰቦች ብቻ ሳይሆን ለሟች ወገኖችም ጭምር የሚከፋፈል ነው የሚሆነው:: ምክንያቱም የሟች ወገኖች በቂም በቀል ተነሳሳተው የገዳይ ወገኖች ላይ ጥቃት እንዳይፈጸሙ የሚከፈለው ካሳ ለእያንዳንዱ ሰው እንዲዳረስ የሚደረግበት ሂደትም አለ::

በዚህ የሕይወት ካሳ አወሳሰን ላይ የሀገር ሽማግሌዎች የማይተካ ሚና ቢኖራቸውም በዋናነት ግን አባገዳዎች ትልቁን ድርሻና ስልጣን አላቸው:: ይህም የሚካሄደው ሁለቱም ወገኖች የተግባቡበት የሕይወት ካሳ ክፍያ ለአባገዳና ለአባቦኩ ለውሳኔ ያቀርባሉ:: ስምምነታቸው በሚገባ ከታየ በኋላ የተለያዩ ሥርዓቶች በመፈጸም እርቁ ፍጻሜ እንዲያገኝ የሚያደረጉበት ሂደቶች ይፈጸማሉ::

የእርቁ ዕለት የሰው ሕይወት ያጠፋ ሰው (ገዳይ) የፈጸመው ድርጊት ተገቢ እንዳልሆነና በፈጸመው ድርጊት ማዘኑንና መጸጸቱን በተለያየ መንገድ መግለጽ ይጠበቅበታል:: ይህንንም አሮጌ፤ አዳፋ (ቆሻሻ) አሊያም የተበጣጠሱ ልብሶችን በመልበስ፣ ፊቱን ጭቃ በመቀባት እና በመሳሳሉ ሁኔታ ይገልጻል:: አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ እጅ ወደኋላ ታስሮ እንደሚቀርብ ጭምር ይነገራል::

በእርቅ ሥርዓቱ ከሚፈጸሙት ሥርዓቶች መካከል በዋነኛነት ሳይጠቀስ የማይታለፈው የመሀላ ሥርዓት ይፈጸማል:: መሀላውም ሥርዓቱ ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት በበዳይና ተበዳይ መካከል ዳግም ጸብ እንዳይከሰትና እርቁን ለማጽናት በማሰብ ነው:: በመሀላው ደግሞ እንዲህ አይነት ነገር አልፈጸምም ከፈጸምኩ ደግሞ ይህ ይሁንብኝ ይደረግብኝ አይነት የሚሉ ሀሳቦችን የያዘ ነው:: እንዲህ አይነት ከባድ መሀላዎች ያሉ ስለሆነ መሀላው ካልተፈጸም የተናገረው ነገር እንደሚፈጸምበት ይቆጠራል:: መሀላው ከተፈጸመ በኋላ ሁለቱ ወገኖች መሀላውን በማሰብ ዳግም ግጭት ውስጥ እንዳይገቡ የሚያደርግ ሲሆን፤ የሟች ወገኖች ይህ መሀላ ችላ ብለው መልሰው ወደ ቂም በቀል እንዳይገቡ ያደርጋል ተብሎም ይታመናል::

ከዚህ ቀጥሎም የጉማ አከፋፋል ጊዜና ሁኔታ ይስወናል:: የሰው ነፍስ ያጠፋው ሰው

(ገዳዩ)፤ የተወሰነበትን የሕይወት ካሳ ለመክፈል በራሱ ካለው ንብረት ላይ መክፈል ቢችልም እንኳን ከራሱ ንብረት ላይ ብቻ እንዲከፍል አይፈቀድለትም:: ምክንያቱ ያጠፋው ነፍስ መመለስ ባይቻል እንኳን ጥፋተኛነቱን አውቆ ከልቡ እንዲሰማውና እንዲጸጽት የሚያደርጉ አካሄዶች መከተል ይጠበቅበታል::

በመሆኑም የሰው ሕይወት የቀጠፈው ሰው (ገዳይ)፤ በተወሰነለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ወጥቶ ወርዶ እና ለፍቶ ወገኖቹንና የአካባቢውን ማህበረሰብ ስለጉዳዩ በመንገር ጉዳዩን እንዲያወቁ እያደረገ እንዳለም ይደረጋል:: በልመና ሂደቱም የሰው ሕይወት የቀጠፈው ሰው (ገዳይ)፤ ሁለት እጆቹ በሰንሰለት ታስረው ከወገኖቹ ጋር በመሆን በገበያ ቦታዎች እና ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ሁሉ በመዞር ‹‹የሰው ሕይወት በእጄ ላይ ጠፍቶ ነው›› እባካችሁን እያለ ሰዎችን በመማጸን ይለምናል:: ይህ የሚሆንበት ምክንያትም የሰው ሕይወት ያጠፋው ሰው በድርጊቱ አብዝቶ እንዲጸጸትና እንዲቆጨው ለማድረግ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች እሱን ለሚመለከቱት ሰዎች የሰው ነፍስ ማጥፋት ኃጢያት መሆኑና ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ ለማስገንዘብ በማሰብ ነው::

በገዳ ሥርዓት ከጦርነት ውጭ ያለአግባብ የሰው ሕይወት ያጠፋ ሰው ጉማ ካላወጣ ከማኅበራዊ ሕይወት እንዲያገለግል ይደረጋል፤ ስለዚህ በኦሮሞ ሥርዓት ጉማ መክፍል ግዴታ ነው:: የሚከፍለው ካሳ የጠፋው የሰው ሕይወት ዋጋ የሚተካ ተብሎ ሳይሆን በሁለቱ ወገኖች መካከል እርቅን እንዲኖር በማድረግ የተሰራው ኃጢያት ማስተሳሰሪያ እና የቀድሞ ዝምድና ወደነበረበት ይመልሳል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው::

ከእርቅ በኋላም በሁለቱም ወገኖች በዳይና ተበዳይ መካከል የዝምድና ሁኔታ ተጣርቶ ዝምድና ከሌላቸውና መጋባት የሚችሉ ከሆነ አንዱ ከሌላ ጋር በጋብቻ እንዲተሳሰር የሚደረግበት ሁኔታ ይኖራል:: ይህ የሚሆንበት ዋንኛ ምክንያትም በሁለቱ ወገኖች መሀል ያለው ጥላቻ በማራቅ ጥብቅ የሆነ ዝምድና በመፍጠር ትስስር እንዲኖራቸው ለማድረግ ታስቦ ነው::

በተጨማሪም በጉማ እርቅ ሥርዓት የተወሰነ ካሳ ቢከፍል፤ ጉማ የሚሰጠው ለጠፋው ሕይወት ዋጋ ለመስጠት እንጂ፤ የሚከፈለው ካሳ የሚገኘው ሀብት ተፈልጎ አይደለም::

ይህ ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የኦሮሞ ሕዝብ የግጭት አፈታት ሥርዓት ያለው ጠቀሜታ እጅግ የጎላ ነው:: ሥርዓቱ አሁን ላይ እንደሚታየው በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም:: በመሆኑም ጠቀሜታው እንደማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆን እንደሀገር ከፍተኛ በመሆኑ ሌላው ማኅበረሰብ ሊጠቀምበት የሚችል እንዲሆንና ዘመን ተሻጋሪ ሆኖ በደንብ ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የድርሻቸውን መወጣት እንዳለባቸው ያመላክታል::

# የአዕምሮ ህመም ህክምናዎች በጣምራ ሊሰጡ ይገባል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ለአእምሮ ህመም ህክምና ውጤታማነት መድሃኒት፣ የሥነልቦና እና የተሃድሶ ህክምናዎች ሳይነጣጠሉ በጣምራ ሊሰጡ እና ለዘርፉ ተገቢው ትኩረት ሊደረግ እንደሚገባ የአእምሮ ሃኪም መምህርና ተመራማሪ ፕሮፌሰር አታላይ ዓለም ገለጹ፡፡

«የተሃድሶ ህክምና ለአእምሮ ጤና» በሚል መሪ ሃሳብ አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ባካሄደው ውይይት ፕሮፌሰር አታላይ እንደገለጹት፤ የአእምሮ ህመም በአንድ ሀገር ከባድ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጫና የሚያስከትል መሆኑን በመገንዘብ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

የተሃድሶ ህክምና ትኩረት ተሰጥቶት ተቋምና የሠለጠኑ ባለሙያዎች ተመድበውለት ሊተገበር የሚገባ፣ ለአካል ህመም ለተጠቁ ብቻ ሳይሆን በአእምሮ ህመም ለተቸገሩ ሰዎች ጭምር ሊሰጥ የሚገባ የህክምና አይነት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የተሃድሶ ህክምና አገልግሎት አንድን የአካል ወይም የአእምሮ ህመም ችግር ደርሶበት ጉድለት ያጋጠመውን ሰው፣ በአደጋ፣ በሱስ ምክንያት ያጣውን ራሱን ችሎ የመኖርና የመንቀሳቀስ ክህሎቱን እንደገና ለመመለስና ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለማሕበረሰቡ አስተዋጽኦ ማድረግ እንዲችል ለማብቃት የሚደረግ የህክምና ሂደት ነው፡፡

አነስተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት የሚሰጠው የህክምና አይነት በአብዛኛው የመድሃኒት ህክምና ብቻ መሆኑን ጠቅሰው፤ ባደጉ ሀገራት ግን የተሃድሶ ህክምና የተሻለ ትኩረት ማግኘቱን ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ የጤና ህመም ያለባቸው ሰዎች በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና እንደሚጋለጡ በጥናት ተመልክተናል ያሉት ፕሮፌሰር አታላይ፤ በኢትዮጵያ ከችግሩ ስፋት አንጻር እየተሰጠ ያለው የተሃድሶ ህክምና አነስተኛ ነው ብለዋል፡፡

የዓለም ጤና ጥበቃ ሪፖርት የችግሩ መጠን ሰፊ መሆኑን እንደሚያሳክት ጠቅሰው፤ ከሁሉም ሀገራት የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ አነስተኛ ገቢ ባላቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት የትኩረቱ መጠን እጅግ አነስተኛ መሆኑንም ነው ያስገነዘቡት፡፡

ከጤና ጉዳት ጋር ከሚኖሩ ሰዎች መካከል በአእምሮ ጤና ችግር ምክንያት የሚኖሩ ሰዎች ቀዳሚውን ድርሻ እንደሚይዙ የጠቆሙት ፕሮፌሰሩ፤ የአእምሮ ህመም በእድሜና በኑሮ ደረጃ እኩል ከሆኑ ሰዎች መካከል በህመሙ የተያዙ ሰዎች ከ10 እስከ 20 ዓመታት እድሜ ቀድመው ይሞታሉ ብለዋል፡፡

የአእምሮ ህመም አነስተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ትኩረት የማይሰጥበት ምክንያት በቀጥታ ገዳይ ህመሞች ባለመሆኑ ይሁን እንጂ፤ ህመሙ ገዳይ ለሆኑ የተለያዩ የህመም አይነቶች የማጋለጥ ዕድሉ ከፍተኛ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በዘርፉ በጎ ለውጦች መኖራቸውን የጠቆሙት ፕሮፌሰር አታላይ፤ በአዲስ አበባ ብቻ ይሰጥ የነበረው አገልግሎቱ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በሁሉም የጤና ተቋማት ማስፋፋት መቻሉን፣ የጤና ባለሙያዎች ቁጥር ማደጉን ተናግረዋል፡፡ ከችግሩ ስፋት አኳያም የአእምሮ ህክምና ብዙ ቀሪ ሥራዎች እንዳሉበት አመልክተዋል፡፡

# ኢትዮጵያ በአቪዬሽን ደህንነት ዘርፍ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የኦዲት ባለሙያዎች ሲደረግ የቆየው የኢትዮጵያ አቪዬሽን ደህንነት ኦዲት ውጤት በትናንትናው ዕለት ይፋ ሆኗል።

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የሲቪል አቪዬሽን ደህንነት መምሪያ ዳይሬክተር አስራት ቀጀላ ውጤቱን አስመልክቶ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ከግንቦት 26 እስከ ሰኔ ስድስት ድረስ ለተከታታ አስር ቀናት የዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ድርጅት የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ደህንነት ደረጃን ኦዲት አድርጓል።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ የዓለም አቀፉ የአቪዬሽን ድርጅት የኦዲት ባለሙያዎች በሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርትን በስፋትና በጥልቀት ገምግመዋል። እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ኤርፖርቶች ከሲቪል አቪዬሽን ደህንነት፣ ከዓለም አቀፉ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት አኳያ ምን ያህል ውጤታማ ናቸው የሚለው ተገምግሞ ጥሩ ውጤት ተገኝቷል።

ከቴክኖሎጂ፣ ከመሠረተ ልማት፣ ከአዋጅና መመሪያ አንጻር ባደረጉት ግምገማ መሠረት ምንም አይነት ወሳኝ የሚባል የደህንነት ስጋት የሌለበት መሆኑን ማረጋገጣቸውን ገልጸዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ዓለም አቀፉ የአቪዬሽን ድርጅት ለ193 ሀገራት እኩል ፖሊሲ፣ መመሪያና አሠራሮችን ያወጣል። አባል ሀገራቱ የመተግበር ግዴታ አለባቸው፤ ድርጅቱም ኦዲት አድርጎት ውጤት ይገልጻል። ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ከ2012 በኋላ በጦርነት፣ በኮቪድ 19ኝና በሌሎች ምክንያቶች ለአስራ ሁለት አመት ኦዲት ሳትደረግ ቆይታለች።

ከ12 ዓመት በኋላ ከአዋጁና መመሪያ ጀምሮ ኢትዮጵያ ለአቪዬሽን ዘርፉ የሰጠችው ትኩረት ለአስር ተከታታይ ቀናት በጥልቀት ተዳሶ እንደ ሀገር የሚያኮራ ውጤት ተገኝቷል ብለዋል።

በኦዲት ውጤት መሠረት ኢትዮጵያ ምንም አይነት የአቪዬሽን የደህንነት ስጋት የሌለባት መሆኑን በሁሉም ኤርፖርቶች ተረጋግጧል። የመረጃና ደህንነት ቢሮ የአቪዬሽኑን ዘርፍ ከማንኛውም ጣልቃ ገብነት ለመከላከል በተቀመጠው ዓለም አቀፍ መመሪያ መሠረት ትኩረት ሰጥቶ ማሻሻያዎችን ማድረጉን ውጤቱ ያመለክታል። በኦዲት በተገኘው ውጤት የአፍሪካና የኢትዮጵያ ኩራት የሆነው አየር መንገድ በከፍተኛ ውጤትና አስተማማኝነት በረራውን እንዲቀጥል የሚያስችል ነው።

ውጤቱ ለኢትዮጵያና ለአየር መንገዱ ትልቅ ውጤት ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩ ሌሎች አየር መንገድ ኦፕሬተሮች ያለምንም ስጋት በኢትዮጵያ ለመሥራት ከፍተኛ በር ይከፍታል። እንዲሁም የኢትዮጵያ የአየር መንገድ የበረራ አድማሱን ለማስፋት ያለምንም ተጨማሪ የደህንነነት ማረጋገጫ መብረር ያስችለዋል።

ውጤቱ በብዙ መመዘኛው ትልቅ እድል ያመጣ መሆኑን የገለጹት አቶ አስራት፤ በኦዲት መሠረት የአቪዬሽን ደህንነት አስተማማኝ ሁኔታ መገኘቱ ለኢትዮጵያ የቱሪዝም እድገት፣ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚና በፖለቲካው ዘርፍም ትልቅ ውጤት ያስገኘ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ለውጤቱ መሳካት መንግሥት ለዘርፉ የሰጠውን ልዩ ትኩረት እንደሚያሳይ ጠቁመው፤ የተሰጡ አስተያየቶች ቀላል በመሆናቸው በአጭር ጊዜ ይስተካከላሉ ሲሉ ጠቁመዋል።

ወደፊትም የኢትዮጵያን አየር መንገድ እድገትና ቀጣይነት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስቀጠል የተጀመሩ የቴክኖሎጂ ሥራዎችን አጠናክሮ የማስቀጠልና የአቪዬሽን አዋጅን የማሻሻል ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

# በኦጋዴን ከ21 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የተፈጥሮ ጋዝ እንዳለ ተረጋግጧል፡፡

በአካባቢው 19 ጉድጓዶችን በመቆፈር በተደረገ ዳሰሳ 21 ቢሊዮን 336 ሚሊዮን የተፈጥሮ ጋዝ ተገኝቷል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በክልሉ ኦጋዴን አካባቢ ያለውን ሀብት በተገቢው መልኩ ለመጠቀም በስፋት ሥራዎች መሠራታቸውን አብራርተዋል፡፡

በአካባቢው ትልቅ ሀብት እንዳለ መረጋገጡን ያነሱት አቶ ሚሊዮን ፤ በተጨማሪም በኢትዮጵያ በስድስት ቦታዎች ላይ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት መኖሩን ተናግረዋል፡፡ ኦጋዴን፣ መቀሌ፣ መተማ፣ ደቡብ ኦሞ እንዲሁም ጋምቤላ አካባቢዎች በዋናነት ተጠቃሽ መሆናቸውንም አስገንዝበዋል፡፡

ወደፊት ፍለጋው ተጠናክሮ መቀጠል ከቻለ አሁን ከተገኘው እጥፍ በላይ ማግኘት እንደሚቻል የሚጠቁሙ መረጃዎች እንዳሉም ነው አቶ ሚሊዮን ያመላከቱት፡፡

እንደ አቶ ሚሊዮን ገለጻ፤ በክልሉ የተገኘው የተፈጥሮ ጋዝ በቅርብ ዓመታት ወደ ምርት ለማስገባት ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ሌሎች በፍለጋ ምዕራፍ ላይ ያሉትም በአጭር ጊዜ ውጤታማ የሚሆኑበትን አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

በተጨማሪም የተጀመረው ፍለጋ በሌሎች አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ የሚቀጥል ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የተጀመረውን ሥራ ውጤታማ ለማድረግ ድጋፍና ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

የማዕድን ዘርፍ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍ ለማድረግ ትልቅ ተስፋ ከተጣለባቸው ዋና ዋና ዘርፎች መካከል አንዱ በመሆኑ በተገቢው መንገድ ኪኮኖሚውን እንዲደግፍ ትኩረት መደረጉንም አስገንዝበዋል፡፡

እንደ አቶ ሚሊዮን ገለፃ፤ ለአንድ ሀገር ልማት የተለያየ የኃይል አማራጭ ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ማዕድናት በተገቢው መልኩ ማልማት ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን ከማጎልበት ጎን ለጎን በጂኦ-ተርማል ዘርፍ ያላትን ከፍተኛ አቅም ለኃይል አማራጭ ለማዋል እየሠራች እንደምትገኝ አያይዘው የገለጹት አቶ ሚሊዮን፤ ከክልሎችና ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር ትልልቅ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

በተለይ ጂኦ-ተርማልና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ዘርፎች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ ከመደገፋቸው በተጨማሪ ለወደፊት ከፍተኛ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችሉ ናቸው ብለዋል፡፡

# የውጭ ቀጥተኛ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከገዳ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ኮርፖሬሽን ጋር የተደረገው ስምምነት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እድገት ለማጎልበትና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ በሚደረገው ሂደት ውስጥ አዎንታዊ ሚና ያለው ነው ብለዋል።

ኮሚሽኑ በተለይም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እንዲጠናከር የውጭ ባለሀብቶችን በመሳብ፣ የተመለመሉትን ወደ ተግባር በማሸጋገር እንዲሁም ጠንካራ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በከገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ጉልህ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በቅርቡ የጸደቀውን የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ መሠረት የተከፈቱ አዳዲስ ዘርፎች መኖራቸውንም ኮሚሽነር ዘለቀ ጠቅሰዋል።

ለውጭ ባለሀብቱ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን የሚያሳድጉ ተግባራትንም በማከናወን ላይ እንዳለ የገለጹት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ከገዳ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ጋር የሚደረገው ስምምነትም የዚህ ማዕቀፍ አንዱ አካል መሆኑን ተናግረዋል።

የገዳ ኢኮኖሚ ዞን ወደ ትግበራ መግባት መቻል የኢኮኖሚ እድገትን ለማጎልበትና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ በሚደረገው ሂደት ውስጥ አዎንታዊ ሚና ያለው መሆኑን ተናግረዋል።

የመንግሥትና የግል ኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚዎች እንዲያለሙ የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ እየተሠራ ነው ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ከገዳ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ኮርፖሬሽን የሚደረገው ስምምነት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ ለሀገር ውስጥና የውጭ አልሚዎች ምቹ መደላድል ለመፍጠር፣ ለኢንዱስትሪዎች መስፋፋት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማስፋፋትና የሥራ እድል ፈጠራን ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት አስታውቀዋል።

የገዳ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሞቱማ ተመስገን በበኩላቸው፤ ኮርፖሬሽኑ በአፍሪካ ታዋቂ የኢኮኖሚ ማዕከል ለመገንባት የተቋቋመ መሆኑን ጠቅሰዋል።

መሠረተ ልማት በማሟላት፣ የውጭ ምንዛሬን በማሳደግ፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በመሳብና ሰፊ የሥራ እድል በመፍጠር የኢኮኖሚ እድገት እንዲፋጠን እየሠራ እንዳለም ገልጸዋል።

ስምምነቱም ኢንቨስተሮች ያለምንም እንግልት የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል በማለት፣ በሶስት ሺህ 114 ሄክታር መሬት ላይ ልማት ለመጀመር ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑ ተናግረዋል።

የገዳ ኢኮኖሚ ዞን በኦሮሚያ ክልል ከአዳማ ከተማ አስተዳደርና ከሉሜ ወረዳ ለመጀመሪያ ዙር ሶስት ሺህ 114 ሄክታር መሬት በማግኘት በ120 ሚሊዮን ዶላር መነሻ ካፒታል ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ለመሆን ጥያቄውን ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በማቅረብ፤ ስያሜ ለማግኘት በሕግ የተቀመጡ መስፈርቶች ማሟላቱን፤ እንዲሁም አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅቶች በመጨረስ እኤአ ሐምሌ 13 ቀን 2022 የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜን ማግኘት እንዳቻለ ተጠቅሷል።

# ሚኒስቴሩ ለጸረ ተባይ ርጭት የሚውሉ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለአውሮፕላኖቹ ግዢ 10 ሚሊዮን ዶላር ወጪ እንደተደረገባቸው የተናገሩት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ባለፉት ጊዜያት በቂ የርጭት አውሮፕላንኖች ባለመኖራቸው የአንበጣ መንጋና የግሪሳ ወፍ የመከላከል ሥራውን አዳጋች እንዳደረገውና በምርት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሲደርስ መቆየቱን አንስተዋል፡፡

የተገዙት አውሮፕላኖች በፀረ ሰብል ተባዮች እና አዕዋፍ የሚደርስ የምርት ብክነትን በመቀነስ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዱ መሆናቸውን አስገንዝበዋል፡፡ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ጠቀሜታቸው የጎላ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

የግብርና ሥራውን ለማዘመን የሚደረገው ጥረት ውጤታማ ለማድረግ በቀጣይ ተጨማሪ አውሮፕላኖችን ለመግዛት ታቅዷል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም አውሮፕላኖቹ ካላቸው አቅም የተነሳ ፀረ- አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን የመርጨት እንዲሁም የሰደድ እሳትን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር ላይ እንደሚሰማሩ ገልጸዋል፡፡

በዚህም በሀገር ውስጥ ምንም አይነት ችግር በማይኖርበት ጊዜ አውሮፕላኖቹን ለጎረቤት ሀገራት በማከራየት ገቢ በማግኘት የወጣወን ወጪ ለመመለስ መታቀዱንም ገልጸዋል፡፡

በብሔራዊ አየር መንገድ ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት አውሮፕላን የማስተዳደሩ ተግባር ኃላፊነት ለማህበርሩ መስጠቱን ተናግረዋል፡፡

የብሔራዊ አየር መንገድ ኃ/የተ/የግል ማህበር ሥራ አስኪያጅ ካፒቴን አበራ ለሚ በበኩላቸው፤ በግብርና ሚኒስቴር የተገዙት አውሮፕላንኖች በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቅረፍ እንደሚያግዝ ገልጸዋል፡፡

ማህበሩ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን የአየር ኦፕሬተር ፈቃድ ከኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን አግኝቶ በሥራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አውሮፕላኖቹን የማስተዳደር፣ የሚያበሩ ባለሙያዎችንና ቴክኒሻኖችን እንዲሁም አስፈላጊውን የሰው ኃይል የማሟላት ሥራን እንደሚሠራ ካፒቴን አበራ ገልጸዋል፡፡




አቶ በላይነህ ንጉሴ

የኬሚካል ርጭት ሥራ በብሔራዊ አየር መንገድ አማካኝነት እንዲከናወን በተገባው ስምምነት መሠረት ሥራ ማስጀመሪያ ፕሮግራም ሰኔ 8 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚከናወን አመላክተዋል፡፡



ካፒቴን አበራ ለሚ

# ስፖርት



## በተለያዩ ርቀቶች ኢትዮጵያን በኦሊምፒክ የሚወክሉ አትሌቶች ዛሬ ይታወቃሉ

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በፓሪስ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶችን ለመምረጥ የማጣሪያ (የሰዓት ማሟያ) ውድድሮችን ዛሬ በስፔን ማላጋ ያካሂዳል:: በመጪው ነሐሴ ወር/2016 ዓ.ም በሚደረገው ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን ከ800 ሜትር እስከ ማራቶን ባሉት ርቀቶች የሚወክሉ አትሌቶች ተመርጠው ከሚያዚያ ወር መጨረሻ አንስቶ ወደ ዝግጅት መግባታቸው ይታወቃል:: ዛሬ ማላጋ ላይ በሚደረገው የሰዓት ማሟያ ውድድርም የዓለም አትሌቲክስ የኦሊምፒክ ተሳትፎ ያስቀመጠውን ሰዓት የሚያሟሉ የመጨረሻዎቹ አትሌቶች የሚለዩበት ይሆናል::

በፌዴሬሽኑ አዘጋጅነት የሚካሄደው ይህ የማጣሪያ ውድድር በሴትና ወንድ 10ሺ ሜትር እንዲሁም በወንዶች 800 ሜትር እና የ1ሺ500 ሜትር ይካሄዳል:: በሌሎች ርቀቶች ዓመቱን ሙሉ በሚከናወኑ ርቀቶች አትሌቶች ባስመዘገቡት ሰዓት መሰረት ለብሄራዊ ቡድን የሚመረጡ ሲሆን፤ በ10ሺ ሜትር ርቀት ደግሞ ውደድሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተመናመኑ በመሆናቸው አትሌቶችን ለመምረጥ የዛሬው የማጣሪያ ውድድር አስፈልጋል:: በመሆኑም ዓለም አቀፉ የአትሌቲክስ ተቋም ያስቀመጠውን ሰዓት ለማስመዝገብ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች እርስበርስ የሚፎካከሩ ይሆናል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመካከለኛ ርቀት ሴቶች ኢትዮጵያ ሳይጠበቅ ተፎካካሪና ውጤታማ በመሆን ላይ ትገኛለች:: በአንጻሩ በወንዶች 800 እና 1ሺ500 ሜትር ርቀቶች በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የአትሌቶች ተሳትፎና ውጤታማነት እየቀነሰ መምጣቱ ታይቷል:: እስካሁን ድረስም ለፓሪሱ ኦሊምፒክ ተሳትፎ የሚያበቃ ሰዓት መመዝገብ አልቻለም:: ይህም ‹‹ኢትዮጵያ ፓሪስ ላይ በመካከለኛ ርቀት በወንዶች ተወካይ ታገኝ ይሆን?›› የሚል ጥያቄ ፈጥራል:: የዛሬው የማጣሪያ ውድድርም ለዚህ ጥያቄ መልስ ይኖረዋል::



የሚኒማ ማሟያ ውድድሩ በፓሪስ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶች ይለዩበታል፤

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በእነዚህ ርቀቶች ከኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ጋር በመሆን አሯሯጮችን በመመደብ ሰዓቱ ተሟልቶ ኢትዮጵያን የሚወክሉ አትሌቶችን ለመለየት ማጣሪያውን ማዘጋጀቱን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዮሃንስ እንግዳ ገልፀዋል:: በማጣሪያው ላይ ከእጩ አትሌቶቹ ባለፈ ሰዓት ለማሟላት ፍላጎት ያላቸው አትሌቶችም ወጪያቸውን ራሳቸው ሸፍነው እንደሚሳተፉ ታውቋል::

ከማራቶን ውጪ ባሉት ርቀቶች የሰዓት ማሟያ ጊዜ ገደቡ ገና ቢሆንም የዛሬው ማጣሪያ የ10ሺ ሜትር ተሰላፊ አትሌቶች ተለይተው ወደመጨረሻው የኦሊምፒክ ዝግጅት ይገባሉ:: በመካከለኛ ርቀት አትሌቶች ባላቸው ሰዓት መሰረት ሚኒማ ሊያሟሉ ይችላሉ በሚል ተመርጠው ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተዋል:: የዓለም አትሌቲክስ ለ800 ሜትር 1፡44.70 እንዲሁም ለ1ሺ500 ሜትር 3፡33.50 የሆነ ሰዓት ያስቀመጠ ሲሆን፤ ይህም ሰዓት በየጊዜው እየጠበበ ስለመምጣቱ ለመረዳት ይቻላል:: በዛሬው ማጣሪያ ይህ የማይሟላ ቢሆንም በማህበሩ እስከተገደበው የሰዓት ማሟያ ጊዜ ድረስ የሚኖሩ ሌሎች ውድድሮችን በመዝጋት ወደመጨረሻው የዝግጅት ምዕራፍ የሚገባ መሆኑንም ኃላፊው አስረድተዋል::

ነገር ግን በቀጣይ በሚካሄዱት ውድድሮች ላይ የመግቢያ ሰዓት ላይሟላም ስለሚችል የዛሬው የማጣሪያ ውድድር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል:: ቡድኑ ሆቴል ገብቶ ዝግጅት ከጀመረ ከአንድ ወር በላይ ስላስቆጠረ ኢትዮጵያን ወክለው በኦሊምፒክ የሚካፈሉ አትሌቶች ይኖራሉ ተብሎም ይጠበቃል:: አትሌቶች በኦሊምፒክ ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን ሰዓት በተለያዩ ውድድሮች ላይ እንደሚያስመዘግቡ ይታወቃል፣ በዚህም በሃገርም ሆነ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ዘመናዊ (ኤሌክትሮኒክስ) ሰዓት መመዝገቢያ መያዝ ያለባቸው ሲሆን፤ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ግን ለዚህ ምቹ ሊሆኑ አልቻሉም:: ኢትዮጵያ ከምትገኝበት የቦታ አቀማመጥ ጋር ተያይዞ ፈጣን ሰዓት ማስመዝገብ ከባድ በመሆኑ ምክንያት ባለፉት ዓመታት በሄንግሎ የሰዓት ማሟያ ውድድር ሲደረግ ቆይቷል::

ባለፈው ዓመት የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የማጣሪያ ውድድሩን ሃዋሳ ላይ ለማካሄድ ታቅዶ ዕውቅና ቢገኝም ሚኒማ ማሟላት ባይቻልስ የሚለው ስጋት ፌዴሬሽኑ በድጋሚ ፊቱን ወደ ውጪ ሃገራት እንዲያዞር አድርጎታል:: በተለይ የ10ሺ ሜትር ርቀት ሚኒማ በየጊዜው እየተቀነሰ መሆኑን ተከትሎ ሰዓቱ ሊሟላ በሚችልበት ስፍራ ማጣሪያውን ከማድረግ ውጪ አማራጭ ባለመኖሩ የዛሬውን ውድድር ስፔን ላይ ለማድረግ መገደዱንም ኃላፊው አስገንዝበዋል::


## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር አዩ - 07/01/2016

በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን የአርባ ጉጉ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒዬን ኃላ/የተወሰነ በ2016 የበጀት አመት ለዩኒዬኑ አባል ለሆኑ ህብረት ስራ መህበራት የግብርና ግብዓት ለማጓጓዝ የሚያገለግል ሲኖ ትራክ የጭነት መኪና በሻንሲ እና ተሳቢ መኪና ለየብቻው በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሰረት በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች:-**

1. በዘርፉ ህጋዊ የታደሰ ንግድ ፍቃድ (ቲን ነምበር) ያላቸው፤ የዘመኑን ግብር የከፈሉ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተጫራቾች ዋጋ ሞልተው የሚያቀርቡበት የጨረታ ሰነድ ጋር ተያይዞ በቀረበው ሰነድ መሰረት ቫትን ጨምሮ መሆን አለበት፡፡
3. ተጫራቾች አዲስ ሲኖትራክ 400 HP 2023 ምርት መኪና በሻንሲ በጨረታው ሰነድ የመሙላት ሀላፊነት አለበት፡፡
4. ተጫራቾች አዲስ ተሳቢ መኪና በጨረታው ሰነድ ላይ የመሙላት ሃላፊነት አለበት፡፡
5. የጨረታው ሰነድ የማይመለስ ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) በዩኒዬኑ ሂሳብ ቁጥር 1000075161127 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ በማድረግ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት አዳማ ከተማ ታደሰ አበበ ህንፃ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሬቻ ቅርንጫፍ ጀርባ በሚገኘው ቢሮ የዩኒዬኑ ንብረት ክፍል ሃላፊ በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
6. ጨረታው የሚቆየው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 (አስር) ተከታታይ የስራ ቀናት ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡
7. ጨረታውተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ11ኛው ቀን ከቀኑ 8:00 ሰዓት ተዘግቶ፤ 8፡30 ሰዓት አዳማ ከተማ ታደሰ አበበ ህንፃ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሬቻ ትርንጭፍ ጀርባ ይከፈታል፡፡
8. እያንዳንዱ ተጫራች ለእያንዳንዱ መኪና 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) የጨረታ ማስከበርያ ሲፒኦ በአርባ ጉጉ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒዬን ኃላ/የተወሰነ ስም በባንክ አሰርቶ ማቅረብ አለበት፡፡
9. ተጫራቾች ከተሰማሩበት የንግድ ስራ ዘርፍ ውጭ በሆነ ንግድ ፈቃድ መወዳደር አይችልም፡፡
10. ዩኒዬኑ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ስበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር**፡- 09-12-30-72-20/ 09-21-09-68-80/ 09-17-03-43-43

**አርባ ጉጉ የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒዬን ኃላ/የተወሰነ**

## ዓለም አቀፍ ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የሚፋቁ የሎተሪ ቲኬቶች 64,000,000 (ስልሳ አራት ሚሊዮን) ባርኮድድ ቢንጎ ባለ ብር 5 ሎተሪ ቲኬቶች በማሳተም በግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ ውድድር መሠረት ፍላጎትና ልምድ ያላቸውን አታሚ ድርጅቶችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ማሳተም ይፈልጋል፡፡

ስሰዚህም በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ሁሉ ይህ ዓለም አቀፍ ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሐምሌ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ለዚሁ ስራ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ከብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ዋና መስሪያ ቤት አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01፣ ነባሩ ህንፃ 2ኛ ፎቁ ቢሮ ቁጥር 31 በስራ ቀናት ከሰኞ እስከ ዓርብ፤ በስራ ሰዓት ከ2፡30 እስከ 6፡30 ሰዓት እና ከ7፡30 እስከ 11፡30 ሰዓት ድረስ በመቅረብ የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈልና በመግዛት መወዳደር ይችላሉ፡፡

ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ማስያዝ ያለባቸው ብር 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) በሲፒኦ ወይም ተመጣጣኝ የሆነና በቀላሉ ሊመነዘር የሚችሉ የገንዘብ አይነት ከጨረታ ሰነዳቸው ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

የጨረታ ማስከበሪያ /ቢድ ቦንድ ጋራንቲ/ ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ በአንዱ ማሲያዝ ይቻላል፡፡

ሀ. በጥሬ ገንዘብ

ሰ. ከታወቀ ባንክ በተዘጋጀ ሲፒኦ ወይም

ሐ. ከታወቀ ባንክ በሁኔታ ላይ ያልተመሠረት የባንክ ጋራንቲ ዋስትና

ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውንና የጨረታ ማስከበሪያውን በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ የቴክኒካልና ፋይናንሻል ሰነድ የያዘ አንድ ዋናና አንድ ቅጂ ለየብቻው በፖስታ በማድረግና በማሸግ በፅሁፍ በመለየት እስከ ሐምሌ 23 ቀን 2016 ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ለዚሁ ስራ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

ጨረታው ሐምሌ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዕለቱ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሐምሌ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡15 ሰዓት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ዋና መስሪያ ቤት አዲሱ ህንፃ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 9 ይከፈታል፡፡

አስተዳደሩ ስለጨረታው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 011-126-78-16 ደውሎ መረዳት ይቻላል፡፡

**ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር**